## ምዕራፍ ፭

## ዘልደት ምንባብ

፩ በስመ እግዚአብሔር ዘይተዋሐድ በት ሥልት፡ ዘይሤለስ በተዋሕዶት፡ ኅቡረ ህሉና ዕሩ የ መለኮት፡ ዘኢይትበሀሉ ፫ አማልክት፡ አላ ፩ አምላክ እስመ እትዛን በጽምረት፡ወድሙራን በአ ሐቲ ሥምረት፡ እንጡሉዓን በመብረቀ ስብሐት ወግልቡባን በእሳት፡ ዘኢይቀድም ፩ እምካልዑ ወካልዑ እምሣልሱ ኢመጠነ ሩፀተ ነፋሳት ወኢ መጠነ ቅጽበተ አዕይንት፡ ዘአሐደ ይሰገድ እም ኅበ ሰብእ ወመላእክት፡ ሎቱ ግናይ ለቀዳማዊ ዘእንበለ ጥንት፡ ወደኃራዊ ዘእንበለ ተፍጻሜት፡፡ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

፪ ንጽሐፍ እንከ ዘለፋሁ ለፎጢኖስ ዘይቤ ለፌ እማርያም ህላዌሁ ለክርስቶስ ወአኮ እምከሀ ዘሀሉና አብ፡፡ ለፎጢኖስ ወለአርዮስ ወለ ስብልያኖስ አሐቲ ፍትወተ ኅሊናሆሙ፡፡ ወእመ ሰ በአፉሆሙ ኢትብሩ ፍካሬ ሃይማኖት ወበዓይነ ልቡናሰ ይትናጸሩ ለአእክዮ ህላዌ ወለአሕጽጾ ክዋኔሁ ለወልድ እምአብ፡፡

፫ አርዮስ ይቤ ፍጡር ውእቱ ክርስቶስ ዘተወልደ እማርያም በእንተ መድኃኒትነ፡ እስመ ይትሔዘቦ ልቡ በከመ ተፈጥረ አዳም እመሬተ ምድር፡፡ወበከመ ተፈጥረት ሔዋን እምዐፅመ ገቦ ሁ ለአዳም፡፡ ወከማሁ ተፈጥረ ክርስቶስ እማኅ ፀነ ድንግል ወተወልደ በእንተ መድኃኒትነ ይቤ፡፡ ናሁኬ አርአየ ፍና ነገሩ ከመ በትእዛዘ አብ ተፈጥረ እማርያም ድንግል፡፡

፬ ስብልያኖስ ይቤ አብ ከመ ብእሲ ወልድ ከመ ንባብ ልሳኑ ወመንፈስቅዱስ ከመ እስትን ፋሰ አፉሁ፡፡ወበእንተዝ ይቤ ፩ ገጽ፣ግጻዌሰ ባሕ ቲቱ አቀመ በአብ ወለወልድኒ ረሰዮ ከመ እንተ ንባብ ዘበእዝን ይደምጽ ወኢያስተርኢ ለዓይን ፡፡ወለመንፈስቅዱስኒ ረሰዮ ከመ እስትንፋሰ አፍ ዘኢይትከሀል ለነጽሮ ወኢይትአመር ኅበ ዓይ የሐውር፡፡

፭ ወከመ ቦቱ መልክዕ ለወልድ ወለመ ንፈስ ቅዱስ በከመ መልክዐ አብ አብጻሕነ ስምዐ መጻሕፍት፡፡ወሀሎ ጽሑፍ ውስተ መጽሐፈ ዘለፋሁ፡፡ፎጢኖስ ይቤ ለፌ እማርያም ክዋኔሁ ለወልድ እንዘ ይትሔዘብ ውእቱኒ ከመ ቃለ ገብርኤል ዘመልእክተ አብ ተፀንሰ እማርያም ወኢይቤ ወልድ ዘሀልው ምስለ አብ ተሰብአ እማርያም በብሥራተ ገብርአል መልአክ፡፡ ናሁኬ ኅበረ ግዕዘ እበዶሙ ለሠለስቲሆሙ ኵሎሙ አረዩ ወኅቡረ ዐለዉ፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## የልደት ምንባብ

፩ በሦስትነት አንድ በአንድነትም ሦስት በሚሆን በባሕርይ አንድ በሚሆን በመለኮትም በሚተካከል በእግዚአብሔር ስም፡አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አይባሉም፡በመዋሀድ የተ ያያዙ በአንዲት ፈቃድም የሚተባበሩ በምስጋና መብረቅ የተጋረዱ በሚነድድ እሳትም የሚሸፈ ኑ ናቸው፡፡አንዱ አንዱን ሁለተኛውም ከሦስተ ኛው አይቀድመውም የነፋሳት ሩጫን ያህል የዓ ይን ጥቅሻም ያህል ከሰዎችና ከመላእክት ዘንድ በአንድነት የሚሰገድለት ለርሱ ምስጋና ይገባል ጥንት ለሌለው ለፊተኛው ፍጻሜ ለሌለው ለኋለ ኛው ለዘላለሙ አሜን፡፡

፪ የክርስቶስ ህልውና ከማርያም ከተወ ለደ ወዲህ ነው ከጥንት ከአብ ህልውና ጀምሮ አይደለም ያለ የፎጢኖስን ተግሣጽ ከእንግዲህ እንጽፋለን፡፡የፎጢኖስና የአርዮስ የስብልያኖስም የኅሊና አሳባቸው አንዲት ናት በሃይማኖት ትም ህርት በአንደበታቸው ባይተባበሩም በልባቸው ዓይን ግን የወልድን ህልውና ለማክፋፋት ክብ ሩን ከአብ ለማሳነስ ይተያያሉ፡፡

፫ አርዮስ ልቡ ተጠራጠረ እኛን ስለ ማዳን ከማርያም የተወለደውን ክርስቶስ ፍጡር ነው አለው፡፡ አዳም ከምድር አፈር እንደተፈጠረ ሔዋንም ከአዳም ጐን እንደ ተፈጠረች እንዲሁ ክርስቶስ እኛን ስለማዳን ከድንግል ማኅፀን ተወለደ እነሆ የነገሩ አካሄድ በሕዝብ ትእዛዝ ከማርያም እንደተፈ ጠረ ያሳያል አለ፡፡

፬ ስብልያኖስ አብ እንደሰው ወልድ እን ደ አንደበቱ ንግግር መንፈስቅዱስም እንደ አፉ እስትንፋስ ናቸው አለ፡፡ስለዚህም አንድ ገጽ ናቸ ው አለ፡ መልክንም ብቻውን በአብ አቆመ ወልድ ንም በጆሮ እንደሚሰማ ለዓይን ግን እንደማይ ታይ ንግግር አደረገው፡፡ መንፈስቅዱስንም ለማ የት እንደማይቻል ወዴት እንደሚሄድም እንደ ማይታወቅ የአንደበት እስትንፋስ አደረገው፡፡

፭ ወልድና መንፈስቅዱስ እንደ አብ መልክ ያለ መልክ እንዳላቸው ግን ከመጻሕፍት ምስክርነትን አደረስን በፎጢኖስ የተግሣጽ መጽ ሐፍም ተጽፎ አለ፡፡ፎጢኖስ እርሱ የአብ መልክ ተኛ በገብርኤል ቃል ከማርያም እንደተፀነሰ ቆጥ ሮ የወልድ ህልውናው ከማርያም ወዲህ ነው አለ፡ ከአብ ጋር ያለ ወልድ በመልአኩ በገብር ኤል የምስራች ከማርያም ሰው ሆኖ ተወለደ አላ ለም፡ እነሆ የሦስቱ ሁላቸው የእብደታቸው ጠባ ይ ተባበረ ተካክለውም በደሉ፡፡

፩ ኦ ፎጢኖስ ምንትኑ ረባሕ ለከ ለእመ ታመልኮ ለወልድ ለዘተወልደ እም ብእሲት ለእመ ኢኮነ ውእቱ ፍጹመ ወልደ እግዚአብሔር።ኦ ፎጢኖስ ምንተኑ ረባሕ ለከ ለእመ ታመልኮ ለፍጡር እንዘ ይትሔዘብ ልብከ ከመ ኢሀለው ውእቱ እምቅድመ ዓለም።ኦ ፎጢኖስ ዘነበ ከልብ ዘተሉከ አሰሮ ለአርዮስ ርእሰ ሰልዋን ዘይቤሉ ለፈጣሪ ፍጥረተ።ወአንተኒ ትቤ ለፌ እግርያም ህላዌሁ፡አርዮስ ቀደመከ በዕልወት ወአንተኒ ተለውኮ በጽርፈት። አርዮስ ኮነከ ርእሰ በሙስና ትምህርት ወአንተኒ ኮንከ ዘነበ በሙስና ልብከ እስመ ኀበ ቦአ ርእስ ህየ ይተሉ ዘነብ።

፪ ኦ ፎጢኖስ ተክለ ሐሰት ዘበታሕቱ ኢትደይ ሥርወ ትክለትከ ወበዘላዕሉ ኢትጸገይ ወኢይኩን ባቲ ፍሬ እስከ ለዓለም። ኦ ፎጢኖስ እምአይቴ ሰተይከ ጸዋዐ ሙስና ዘምሉአ ሕምዘ አንኮለሉ ለልብከ በእንባዜ ስሕተት ወከደኖ ለቀራንብቲከ በብዓወ ኃጣውእ። ኦ ፎጢኖስ አርዌ ጸዋግ እምአይቴ ረከበከ ነዓዊ መሪር ወነደፎ ለልብከ በአሕባ ስሕተቱ ዘምሉእ ጽርፈተ ወወደየ ሕምዘ ውስተ ልብከ ወእምዝ ኢኀለይከ ዘትትናገር ወኢያእመርከ ዘትትናበብ።ወትቤ በነገረ ዐመፃ ክርስቶስ ለፌ እግርያም እምኔሰከ ተዓጽዎ ከናፍር ወበህመተ ልሳን እምትንብብ ዘንተ ነገረ።እምኔሰከ ኢወፂአ እምሐቌ አቡከ ወኢረጊፅ በውስተ ማኅፀና ለእምከ እምትንብብ ዘንተ ነገረ። እምኔሰከ ተአጽዎ ማኅፀና ለእምከ ከመ ኢታስተርኢ በሙላድ እምትንብብ ዘንተ ነገረ በከመ ይቤ እግዚእነ በእንተ ይሁዳ እምኔሰ ለውእቱ ብእሲ ሶበ ኢተወልደ። ማቴ ፳፮፥፳፬

፫ እምኔሰከ ከዊነ ሐውልተ ፄው ከመ ብእሲተ ሎጥ ወከዊነ አርዌ ገዳምኒ ከመ ናቡከ ደናጾር እምትንብብ ዘንተ ነገረ።እምኔሰከ ኢሀልዎ እምህልዎ እምትንብብ ዘንተ ነገረ። ኦ ፎጢኖስ ኮንከ ዕንዚራሁ ለሰይጣን ወእስትንፋሰ ውስተ አፉከ በእስትንፋሰ አፉሁ ወኮንከ መሰንቆሁ ለመንፈሰ ሐሰት ወደጕፀከ በድኅንፃሁ ወኮንከ አርጋኖን አጋንንት በዘይገብሩከ ተውኔተ በከመ ፈቀዱ። ኮንከ ሠረገላሁ ለሰይጣን ወተፅዕነ ላዕሌከ እንዘ ይቀንየከ በልጓመ ቅኔሁ ፀመደከ ከመ አባዕር ወአንበረ አርዑቶ ውስተ ክሳድከ። ወአውጽአከ እምግብርናተ ሜጠ ደሙ ለክርስቶስ ወረሰየከ ገብረ ሎቱ። ወይቤለከ ከሐድ ልደቶ ለክርስቶስ ዘእምቅድመ ዓለም ወበል ለፌ እግርያም ከዋኔሁ።ዘፍ፲፱፥፳፮፥፬ ዳን፳፰-፴፯

፬ ትትሔዘብኑ ከመ ቃለ ገብርኤል ተሠገወ እግርያም ወኢተአምርኑ ከመ እግዚአ ገብርኤል ተሰብአ እምኔሃ። ፈነወ ገብሮ ኀበ አመቱ ከመ ያብስራ ብስራተ ሥጋዌሁ። ወይቤላ

፩ ፎጢኖስ ሆይ ከሴት የተወለደው ፍጹም የእግዚአብሔር ልጅ ካልሆነ ብታመል ከው ምን ጥቅም አለህ፡ ፎጢኖስ ሆይ የፍ ጡራንን አኗኗር በማምለክ ምን ጥቅም ታገኛለህ ፎጢኖስ ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በፊት ጀምሮ እንዳልነበረ ልብህ እየተጠራጠረ ፍጡርን ብታ መልከው ምን ጥቅም ታገኛለህ።ፎጢኖስ ሆይ ፈጣሪን ፍጥረት ያለው የከሀዲዎች ራስ የአር ዮስን ፈለግ የተከተልህ የውሻ ጅራት ፎጢኖስ ሆይ አንተም ህልውናው ከማርያም ወዲህ ነው አልህ፡ በክህደት አርዮስ ቀደመህ አንተም በስድብ ተከተልከው አርዮስ በትምህርቱ ጥፋት ራስ ሆነህ አንተም በልብ ጥፋት ጅራት ሆንከው፡ ራስ በገባበት በዚያ ጅራት ይከተላልና።

፪ የሐሰት ተክል ፎጢኖስ ሆይ በታች የመተከልህን ሥር አትዘርጋ በላይም አታብብ ለዘላለሙም ፍሬ አይገኝብህ። ፎጢኖስ ሆይ መርዝን የተመላ የጥፋት ጽዋን ከየት ጠጣኸው በስህተት ልብ ማጣት ልብህን አናወዘው ሽፋሽ ፎቶችህንም በኃጢአት እንጉልኽ ሸፈናቸው።ክፉ አውሬ የሆንህ ፎጢኖስ ሆይ አዳኝ ከወዴት አገኘህ ልብህን ስድብን በተመላ ፍላፃ ወጋው መርዝ ዙንም በልብህ ውስጥ ጨመረ፡ ከዚያም በኋላ የምትናገረውን አላሳብህም አላወቅ ኸውምም በዓመፃ ከንፈሮችም ክርስቶስ ከማርያም ወዲህ ነው አልህ ይህን ነገር ከበት ናገር የከንፈሮች መዘጋት የአንደበትም ድዳነት በተሻለህ ነበር። ጌታችን ስለይሁዳ ለዚያ ሰው ባይወለድ ይሻለዋል እንዳለ ላንተም ይህን ነገር ከምትናገር ከአባትህ ጭን አለመውጣት በእና ትህም ማኅፀን ውስጥ አለመርጋት በመወለድም እንዳትገለጥ የእናትህ አፈማኅፀኗ መዘጋት በተሻለህ ነበር። ማቴ ፳፮፥፳፬

፫ ይህንን ነገር ከምትናገር እንደሎጥ ሚስት የጨው ሐውልት እንደ ናቡከደነፆርም የበረሀ እንስሳ መሆን በተሻለህ ነበር። ይህንን ነገር ከምትናገር ከመኖር አለመኖር በተሻለህ ነበ ር። ፎጢኖስ ሆይ ለሰይጣን መንፈስ እንዚራው ሆንህ በአፉም እስትንፋስ አፍህ ውስጥ ተነፈሰ ።ለሐሰት መንፈስ መሰንቆው ሆንህ፡ በመሰንቆ መምቻው መታህ እንደ ወደዱ ይጫወቱብህ ዘን ድ ለአጋንንት አርጋኖን ሆንህ ለሰይጣን ሠረገላ ሆንህ በላይህ ተጫኘ በአገዛዙም ልጓም እየገዛ እንደበሬዎች ጠመደህ ቀንበሩንም በአንገትህ አስቀመጠ ከኢየሱስ ክርስቶስ የደሙ ቤዛነት አገዛዝ አወጣህ ለራሱ ባሪያ አደረገህ ከዓለም መፈጠር አስቀድሞ የክርስቶስን መወለድ ክደህ ተፈጥሮው ከማርያም ወዲህ ነው በል አለህ። ዘፍ፲፱፥፳፮፥፬ ዳን፳፰-፴፯

፬ የገብርኤል ቃል ከማርያም ሰው ሆኖ እንደተወለደ ትጠራጠራለህን የገብርኤል ጌታ ከእርሷ እንደተወለደ አታውቅምን ሰው የመሆኑን የምስራች ይነግራት ዘንድ ባለሟሉን

ተፈሥሒ ፍሥሕት እግዚአብሔር ምስሌኪ ወና ሁ ትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ::ወትቤሎ እፎኑ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢየአምር ብእሴ:: ናሁኬ እሙነ ተናገረት ወለተ ዳዊት እስመ ኢሰምዓት እምቅድመዝ ዘከመዝ ፅንሰ ወበእንተዝ ኢኄሳ መልአክ በከመ ኄሶ ለዘካርያስ:አላ ይቤላ መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ:: ናሁኬ ፩ ጸታ ሥላሴ ዘይቄድሳ ከመ ትኩን ማኀደረ መለኮት:: ካዕበ ይቤላ መልአክ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ:: ናሁ ዝኒ ካልዕ ጸታ ሥላሴ ዘያጸንዓ ለከዊነ እመ ወልዱ::

፲ ወዓዲመ ይቤላ መልአክ ወዘኒ ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ ወይሰመይ ወልደ ልዑል ወይሁቦ እግዚአብሔር አምላክ መ ንበረ ዳዊት አቡሁ::ናሁኬ ሣልስ ጸታ ዘተወልደ እም ድንግል:: ሉቃ፩፥፴፪-፴፫

፲፩ ወበእንተ መንፈስቅዱስኒ ይቤ ይመ ጽእ ላዕሌኪ ወኢይቤ ይሠገው እምኔኪ:: ወበእ ንተ አብኒ ይቤ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ ወኢ ይቤ መንበረ ዳዊት አቡሁ:: ናሁኬ ሣልስ ጸታ ዘተወልደ እምድንግል:: ወበእንተ መንፈስ ይት ወለድ እምኔኪ::ወበእንተ ወልድሰ ይቤ ወዘኒ ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ ወይሰመይ ወልደ ልዑል::ወበእንተ ልደቱ እምድንግል ይቤ ወይሁቦ እግዚአብሔር አምላክ መንበረ ደዊት አቡሁ እስመ እምዘርአ ዳዊት ይእቲ ማርያም በከመ ይቤ ጳውሎስ ገብሩ ለክርስቶስ ዘተሠ ይመ ሐዋርያሁ ወተፈልጠ ለትምህርተ እግዚአ ብሔር ዘአቅደመ ነጊረ በአፈ ነቢያቲሁ ወበመ ጻሕፍቲሁ ቅዱሳት:በእንተ ወልዱ ዘተወልደ ወመጽአ እምዘርአ ዳዊት በሥጋ ሰብእ:: ወአር አየ ከመ ወልደ እግዚአብሔር ውእቱ በኃይሉ ወበመንፈስቅዱስ:: ዕብ፩፥፩

፲፪ ናሁኬ ያኤምረከ ጳውሎስ ሶበ ይብል ወመጽአ እምዘርአ ዳዊት በሥጋ ሰብእ እስመ ዘቅድመ ሀሎ ሐወጻ ለቤተ ዳዊት ኢሥ ግው እምትካት ተሠገወ እምወለተ ዳዊት:: ወበ እንተዝ ይቤ ወመጽአ እምዘርአ ዳዊት በሥጋ ሰብእ ወአርአየ ከመ ወልደ እግዚአብሔር በኃ ይሉ ወበመንፈስቅዱስ::

፲፫ ካዕበ ይቤ ነቢይ እግዚአብሔርሰ እም ቴማን ይመጽእ ወቅዱስኒ እምደብረ ፋራን ::ፋራን ይተረጐም በጣዕዋ:ወጣዕዋኒ ይተረጐም በንጽሕት ድንግል::ከደነ ሰማያተ ሥኑ :ዝኒ ይተረጐም በኃይለ መለኮቱ ዘዕሩይ ምስለ አቡሁ: ወመልአ ምድረ ስብሐቲሁ::ወዝኒ ይተረጐም በእንተ ገቢረ መንክራቲሁ ዘተሰብከ ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም:: በከመ ይቤ ነቢይ ውስተ ኵሉ

ወደ ሴት አገልጋዩ ላከ እርሱም ደስ ያለሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ አላት:: እር ሷም ወንድ ሳላውቅ እንደምን ይሆንልኛል አለች ው እነሆ የዳዊት ልጅ እውነት የሆነውን ተናገረ ች ከዚያ ጊዜ አስቀድሞ እንዲህ ያለ ፅንስ አልሰ ማችምና::ስለዚህም ነገር መልአኩ ዘካርያስን እን ደነቀፈው አልነቀፋትም መንፈስቅዱስ ባንቺ ላይ ይመጣል አላት እንጂ::ለመለኮት ማደሪያ ትሆን ዘንድ በቅድስና የሚያከብር ከሥላሴ አንዱ አካል እነሆ! ሁለተኛም መልአኩ የልዑል ኃይል ይጋ ርድሻል አላት: የልጁ እናት ለመሆን የሚያፀናት ከሥላሴ ሁለተኛው አካል እነሆ!

፲ ዳግመኛም መልአኩ ካንቺም የሚወለደው ቅዱስ ነው የልዑል ልጅም ይባላል እግዚአ ብሔር አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል አላት ከድንግል የተወለደ ሦስተኛ አካል እነሆ! ሉቃ፩፥፴፪-፴፫

፲፩ ስለመንፈስቅዱስ ባንቺ ላይ ይመጣል አለ ካንቺ ሰው ይሆናል ግን አላለም::ስለ አብም የልዑል ኃይል ይጋርድሻል አለ ካንቺ ይወለዳል ግን አላለም::ስለወልድም ካንቺም የሚወለደው ቅዱስ ነው የልዑል ልጅም ይባላል እግዚአ ብሔር አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰ ጠዋል አለ:: ከአብ ስለመወለዱ የልዑል ልጅ ይባላል ከድንግል ስለመወለዱም እግዚአብሔር አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል አለ: ማርያም ከዳዊት ወገን ናትና::ሐዋርያው የተባለ ለእግዚአብሔር ትምህርትም የተለየ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዩ ጳውሎስ በነቢያቱና በቅዱሳት መጻሕፍት በሰው ሥጋ ከዳዊት ወገን ሰው ሆኖ ስለተወለደ ልጁ መናገርን ያስቀደመ አለ:: በኃይሉና በቅዱስ መንፈሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አሳየ:: ሮዕብ፩፥፩

፲፪ እነሆ ጳውሎስ በሰው ሥጋ ከዳዊት ወገን መጣ ሲል አመለከተህ አስቀድሞ የነበረ እርሱ የዳዊትን ቤት ጉበኛት ከጥንት ጀምሮ ሥጋን ያልለበሰው ከዳዊት ልጅ ሥጋን ተዋሐደ ስለዚህም ከዳዊት ወገን በሰው ሥጋ መጣ አለ በኃይሉና በቅዱስ መንፈሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አመለከተ::

፲፫ ዳግመኛም ነቢዩ እግዚአብሔር ከቴማን ይመጣል ቅዱስም ከፋራን ተራራ ብሎ ተናገረ:: ፋራን በጥጃ ይተረጐማል ጥጃም በንጽ ሀት ድንግል ይተረጐማል፣ክብሩ ሰማያትን ከደነ ይህም ከአባቱ ጋር በተካከለ በመለኮቱ ኃይል ይተረጐማል:: ምስጋናውም ምድርን ሞላት: ይህም ነቢዩ ወደምድር ሁሉ ነገራቸው መጣ እስከ ዓለም ዳርቻም ንግግራቸው ደረሰ እንዳለ

ምድር ወፅአ ነገሮሙ ወእስከ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢቦሙ:: ዕ፺፫÷፫

፲፬ ወካዕበ ይቤ በነቢይ ቡሩክ ዘይመ ጽእ በስመ እግዚአብሔር ባረክናክሙ እምቤተ እግዚአብሔር: እግዚአብሔር እግዚእ አስተርአየ ለነ:: ወዓዲ ይቤ ዘይነብር ዲበ ኪሩቤል አስተ ርአየ::መኑኬ ዘርእዮ ለእግዚአብሔር ዘእንበለ በሥጋዌሁ:: በከመ ይቤሎ ለሙሴ አልቦ ዘርእየ ገጽየ ዘየሐዩ:: ዘጸ፴፫÷፳ መዝ፸፱÷፩፣፻፲፯÷፳፮

፲፭ ዳዊትኒ ይቤ በእንተ ርደተ መለኮት ኀበ ማርያም ወይወርድ ከመ ጠል ውስተ ፀም ር::ወከመ ነጠብጣብ ዲበ ምድር:ወይሠርፅ ጽድ ቅ በመዋዕሊሁ::ወብዙኅ ሰላም እስከ የኀልፍ ወርኅ::ወይኴንን እምባሕር እስከ ባሕር ወእምአ ፍላግ እስከአጽናፈ ዓለም፣ይገንዩ ቅድሜሁ ኢት ዮጵያ ወጸላዕቱኒ ሐመደ ይቀምሑ::ነገሥተ ተርሴስ ወደሰያት አምኃ ያበውኡ:: ነገሥተ ሳባ ወዐረብ ጋዳ ያመጽኡ:: መዝ፸፩÷፮-፱

፲፮ ናሁኬ አግሀደ ቃለ መዝሙር ርደተ ወልደ እግዚአብሔር ኀበ ማርያም ሶበ ይብል ወይወርድ ከመ ጠል ውስተ ፀምር ወከ መ ነጠብጣብ ዘያንጠበጥብ ዲበ ምድር:: ወእም ዝ ያተሉ ወይብል ወይሠርፅ ጽድቅ በመዋዕ ሊሁ:: በከመ ይቤ ጳውሎስ ወማኅለቅቱሰ ለጽ ድቅ አሚን በክርስቶስ::ሠረፀ ጕንደ መስቀል ለምለማ አዕፁቂሁ:: ተሠፀረ ጕንደ ጣዖት ወተቀ ጥቀጠ ግልፎ አማልክት: ሠረፀ በረከተ ወንጌል ወተጸርአ መርገመ ኦሪት:: ሠረፀ መሀይምናን ወተዘርዉ ሰቃልያን:: ሠረፀ ካህናተ ምሥጢር ወተደምሰሱ ገነውተ አማልክት:: ወብዙኅ ሰላም እስከ የኀልፍ ወርኅ እስመ አውራኅሁኒ አውራኅ ሰላም ወዓመታቲሁኒ ዓመታተ ሣህል ወምሕረ ት:: ወይኴንን እምባሕር እስከ ባሕር: ወእምአፍ ላግ እስከ አጽናፈ ዓለም::ዝኒ በእንተ መንግሥቱ ሰፋኒት ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም:: ሮሜ፲÷፬

፲፯ ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ ዝኒ በእንተ አሚነ ሃይማኖቶሙ ዘእንበለ ሐዋርያ :ሰብአ ሮሜ አሕመምዎሙ ለጴጥሮስ ወለ ጳውሎስኒ ወቀተልዎሙ በኅማር ወእምድኅረዝ አምኑ በስብከቶሙ::ሰብአ ህንደኬ ዘሐቁ አነዳሁ ለቶማስ ወወደዩ ወይነ ወጌወ ውስተ ቍስሊሁ እስከ ትውዒ ነፍሱ ወትትመሠው ሥጋሁ እስከ አመ ተሣሃሎ እግዚአብሔር ወፈወሶ ከመ ዘኢ ሐመ:: ወእምድኅረዝኒ ረገዝዎ በ፸ ኵያንው ወቀተልዎ በመለዕልተ ደብር ወእምድኅረዝ አም ኑ በስብከቱ::

፲፰ ወማርቆስ ወንጌላዊ ሰበከ በአድያመ ግብጽ ወእለእስክንድርያ ሰሐብዎ ውስተ ኰኵሕ እንዘ ይብሉ ንስሐቦ ለዳቤላ ዘላህም ወተክዕወ ደሙ ውስተ አስኳት ወሞተ ጽዑረ ሞተ ወእም

እስከዓለም ዳርቻ የተሰበከ ድንቆቹን ስለማድረጉ ይተረጉማል:: ዕ፺፫÷፫

፲፬ ነቢዩ ዳግመኛ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ምስጉን ነው ከእግዚአብሔር ቤት መረቅናችሁ ጌታ እግዚአብሔር ተገለጠልን አለ ከእንደገናም በኪሩቤል ላይ የሚቀመጥ እርሱ ተገለጠ አለ::ለሙሴ ፊቴን አይቶ በሕይወት መቆየት የሚቻለው የለም እንዳለው ሰው በመ ሆኑ ምሥጢር ካልሆነ በቀር እግዚአብሔርን ያየው ማን ነው:: ዘጸ፴፫÷፳ መዝ፸፱÷፩፣፻፲፯÷፳፮

፲፭ ዳዊትም ስለመለኮት ወደ ማርያም መውረድ እንደጠል በፀምር ላይ ይወርዳል በም ድርም ላይ እንደሚንጠባጠብ ጠብታ በዘመኑም ጽድቅ ይበቅላል ጨረቃ እስኪያልፍ ብዙ ሰላም ይሆናል ከባሕር እስከ ባሕር ከወንዞችም እስከ ዓለም ዳርቻ ይገዛል ኢትዮጵያውያን በፊቱ ይገዛ ሉ ጠላቶቹም አመድ ይቅማሉ የተርሴስና የደሴ ቶች ነገሥታት እጅ መንሻ ያቀርባሉ የሳባና የዐ ረብ ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ አለ: መዝ፸፩÷፮-፱

፲፮ እነሆ የዚህ መዝሙር ቃል የእግዚ አብሔር ልጅን ወደ ማርያም መውረድ ገለጠ እንደ ጠል በፀምር ላይ እንደሚን ጠባጠብ ጠብታም በምድር ላይ ይወርዳል ባለ ጊዜ ከዚ ያም አስከትሎ ጽድቅ በዘመኑ ይበቅላል አለ:: ጳውሎስ የኦሪት ጽድቅ ፍጻሜው በክርስቶስ ማመን ነው እንዳለ:: የመስቀል ግንድ በቀለ ቅርንጫፎቹም ለመለሙ የጣዖት ግንድ ተሰነ ጠቀ የአማልክት ምስልም ተሰባበረ የወንጌል በረከት በቀለ የኦሪት መርገም ተወገደ ምእመናን በቀሉ ሰቃዮች ተበተኑ የምሥጢር አገልጋዮች ካህ ናት በቀሉ የአማልክት አገልጋዮች ጠፉ:: ወር እስክያልፍም ብዙ ሰላም ይሆናል ወሮ ችም የሰላም ወሮች ዓመታቱም የይቅርታና የምሕረት ዓመት ናቸው::ከባሕር እስከ ባሕር ከወንዞችም እስከ ዓለም ዳርቻ ይገዛል ይህም በዓለም ዳርቻ ዎች ሁሉ ጸንታ ስለም ትኖር መንግሥቱ የተነ ገረ ነው:: ሮሜ፲÷፬

፲፯ ኢትዮጵያውያን በፊቱ ይገዛሉ: ይህም ያለሐዋርያ ስለማመናቸው ነው የሮማ ሰዎች ጴጥሮስንና ጳውሎስን መከራ አጸኑባቸው በመከራም ገደሉአቸው ከዚህም በኋላ በስብ ከታቸው አመኑ::የሕንድ ሰዎች የቶማስን ቆዳ ገፈፉ በቁስሎቹም ነፍሱ እስክትቃጠል ድረስ ሥጋውም እስክትቆራረጥ እግዚአብሔርም ራር ቶለት መከራ እንዳላገኘው እስኪፈውሰው ድረስ ወይንና ጨው ጨመሩበት ከዚህ በኋላ በስብከቱ አመኑ::

፲፰ ወንጌላዊ ማርቆስ በግብጽና በእስ ክንድርያ አውራጃዎች አስተማረ የላም አውራን እስባለን እያሉ በአለት ላይ ጐተቱት: ደሙ በአደ ባባዮች ፈሰሰ አስጨናቂ ሞትን ሞተ ከዚህ በኋላ

ድኅረዝ አምኑ በስብከቱ:: እንድርያስ ሐዋርያ ቦአ ሀገረ በላዕተ ሰብእ ወደዩ ጎብለ ውስተ ክሳዱ ወሰሐብዎ ውስተ አእባን በሊሐት እስከ ይትቤጻል ሥጋሁ: ወእምድኅረዝ አምኑ በስብ ከቱ:: ወእምዝ ቦአ ውስተ ካልዕ ውእቶሙኒ አዕ ረግዎ ዲበ መስቀል ወኰነንዎ ዐቢየ ኲነኔ እስከ ትወፅእ መንፈሱ ወእምድኅረዝ አምኑ በስብከቱ::

፲፱ ማትያስ ሐዋርያ ቦአ ሀገረ ደማስቆ ገብሩ ሎቱ ዐራተ ዘሐጺን ወአስከብዎ ዲቤሁ አንደዱ እሳተ ላዕሌሁ እስከ ይትሌዐል ነበልባሉ መጠነ ፲ወ፭ በእመት ወነበሩ ከመዝ እንዘ ያነድዱ እስከ ፫ወ፭ ጽባሕ ወአልቦ ዘለከፎ ወእምድኅረዝ አምኑ በስብከቱ::

፳ ዮሐንስ ወንጌላዊ ቦአ ሀገረ እስያ ወነደረ ውስተ ቤተ ሮምና ወአሕመመቶ በቅኔ መሪር እንዘ ይትቀነይ ላቲ በቤተ ምንዳድ ወይእቲኒ እንዘ ትዘብጦ ዘእንበለ ምሕረት ወአጽሐፈት በላዕሌሁ መጽሐፈ ግብርናት ወለስጽባሑ ነበረት እንዘ ታመነድቦ በመቅሰፍት ወእምድኅረዝ አምነት በስብከቱ ሶበ ርእየት መንክራቲሁ:: ወሰብአ ሀገርኒ አንሥኡ መራደ ላዕሌሁ ወላዕለ ዲዮስቆሪዶስ መኰንን ዘአምነ በስብከተ ዚአሁ ወበዝግሐተ መዋቅሕትኒ አመንደብዎ እለ አስ ርሆሙ ምክረ ሰይጣን ወእምድኅረዝ አምኑ በስብከቱ::

፳፩ ፊልጶስኒ ሐዋርያ ቦአ ሀገረ አፍራ ቅያ ወሰበከ ሎሙ በስመ ኢየሱስ ክርስቶስ:: ወእምዝ ነደ ልቦሙ በመዓት ወአዕረግዎ ዲበ መስቀል ወሰቀልዎ ቍልቍሊተ ወቀሠፍዎ ዐቢ የ መቅሠፍተ እስከ ትወጽእ መንፈሱ:: ወዓዲ ፈቀዱ ያንድዱ እሳተ ላዕለ ሥጋሁ ወመሠጦ መልአከ እግዚአብሔር ወእምድኅረዝ አምኑ በስብከቱ::

፳፪ ወንጌላዊ ሉቃስ ቦአ ሀገረ ሮሜ ምስለ ጴጥሮስ መምህሩ ወእምድኅረ ሞቱ ለጴ ጥሮስ ነበረ እንዘ ያጸንዕ ስብከቶ ወያጸንዖሙ ለመሀይምናን::ወእምዝ አኀዞ ኔሮን ንጉሥ ወቀ ሠፎ በጥብጣቤ እስከ ይውኅዝ ደሙ ከመ ማይ::ወአዘዘ ይምትሩ መዝራእቶ ዘየማን እንተ ባቲ ይጽሕፍ መንክራተ እግዚአብሔር ወመንክ ራቲሆሙ ለሐዋርያት::ወበዕለተ ክላሴሁ መተሩ ርእሶ ዘበሰይፍ ወእምድኅረዝ አምኑ በስብከቱ::

፳፫ ማቴዎስ ወንጌላዊ ቦአ ሀገረ ካህናት ወእምድኅረዝ ቦአ አጰንጌ ወፆደ ውስተ በሐውርተ ባርትያ ወመተሩ ርእሶ በመጥባሕት ወእምድኅረዝ አምኑ በስብከቱ::

፳፬ ታዴዎስ ሐዋርያ ቦአ ሀገረ ሶርያ ወገብረ ባቲ መንክራተ:: ወሶበ ዜነውዎ ለወሬዛ ዘብዙኅ ጥሪቱ ከመ ኢይትከሀሎ ጻዲቅ ዘእንበለ

በስብከቱ አመኑ::ሐዋርያው እንድርያስ ሰዎችን ወደሚበሉት ሀገር ገባ በአንገቱ ገመድ አስገብ ተው ሥጋው እስኪቆራረጥ ድረስ በተሳሉ ደንጊ ያዎች ላይ ጐተቱት: ከዚህ በኋላ በስብከቱ አመ ኑ: ከዚያም ወደሌላ ሀገር ሄደ እነርሱም ወደ መስቀል አወጡት በታላቅ መከራም ነፍሱ እስክ ትወጣ ድረስ ሣቀዩት ከዚህም በኋላ በስብከቱ አመኑ::

፲፱ ሐዋርያው ማትያስ ወደ ደማስቆ ሀገር ገባ:: የብረት አልጋ ሠሩለት በላዩም ላይ ነበልባሉ አሥራ አምስት ክንድ ያህል ከፍ ከፍ እስኪል ድረስ በላዩ አስተኝተው እሳት አነደ ዱበት እስከ ሦያ አምስት ቀንም እንዲህ እያነደዱ ተቀመጡ የነካውም የለም:: ከዚህም በኋላ በስብኩቱ አመኑ::

፳ ወንጌላዊ ዮሐንስ ወደ እስያ ሀገር ገባ በሮምናም ቤት ተቀመጠ በማብሰያ ቤት እያገለገለ እርሷም ያለ ምሕረት እየደበደበችው በጽኑ አገዛዝ አሠቃየችው:: በላዩም የባርነት ጽሑፍ አጻፈችበት በየጠዋቱም በግርፊያ እያ ስጨነቀችው ኖረች፣ ከዚህ በኋላ ድንቆቹን ባየች ጊዜ በስብከቱ አመነች የሀገሩ ሰዎች በርሱና በትምህርቱ ባመነው ሹም በዲዮስቆሪዶስ ላይ ቅጥረኛ አስነሱ: ደጃፎችን በመዝጋትም የሰይጣን ምክር አስጨነቁት: ከዚህ በኋላ በስብኩቱ አመኑ::

፳፩ ሐዋርያው ፊልጶስ ወደ አፍራቅያ ሀገር ገባ በኢየሱስ ክርስቶስም ስም ሰበከላቸው: ከዚህ በኋላ ልባቸው በቁጣ ተቃጠለ ወደ መስቀል አውጥተው ዘቀዝቀው ሰቀሉት ነፍሱም እስክትወጣ ድረስ ጽኑ ግርፋትን ገረፉት:: ዳግ መኛም በበድኑ ላይ እሳት ያነዱ ዘንድ ወደዱ የእግዚአብሔር መልአክ ግን ነጠቃቸው ከዚህ በኋላ በስብከቱ አመኑ::

፳፪ ወንጌላዊ ሉቃስ ከመምህሩ ከጴጥ ሮስ ጋር ወደ ሮም ሀገር ገባ: ከጴጥሮስም ሞት በኋላ ትምህርቱን እያጸና ምእመናንንም እያበ ረታ ኖረ:: ከዚያም ንጉሥ ኔሮን ያዘው ደሙ እንደ ውኃ እስኪፈስ ድረስ በጅራፍ ገረፈው:: ከዚያም የጌታችንን ተአምራት የሐዋርያትንም ድንቆች የሚጽፍባትን የቀኝ ክንዱን ይቆርጡ ዘንድ አዘዘ በሚቀላበትም ቀን አንገቱን በሰይፍ ቆረጡ ከዚ ያም በኋላ በስብከቱ አመኑ::

፳፫ ወንጌላዊ ማቴዎስ ወደካህናት ሀገር ገባ ከዚህም በኋላ ወደ አጰንጌ ገባ በባርትያም አውራጃዎች ተዘዋወረ አንገቱን በጐራዴ ቆረ ጡት ከዚያም በኋላ በስብከቱ አመኑ::

፳፬ ሐዋርያው ታዴዎስ ወደ ሶርያ ሀገር ገባ በዚያም ተአምራትን አደረገ ሀብቱ ብዙ ለሆነ ጐልማሳ ገንዘብን በመናቅ ካልሆነ በቀር መጽደቅ

በመንኖ ንዋይ ተምዐ ውእቱ ወሬዛ ወሐነቆ ለታዴዎስ እስከ ፈቀደት ትፃእ ዓይኑ እምንዳቤ ሕንቀት ወበይእቲ ሰዓት ኀለፈ ገመል እንተ ስቍረተ መርፍእ ካዕበ ወሥልሰ በእንተ ዘለፋሁ ለባዕል። ወእምድኅረዝ አምኑ በስብከቱ።

፴፭ ወለኢየሩሳሌም ብዙኅ ደመ ነቢያት ተክዕወ ባቲ እምደመ ኢሳይያስ ነቢይ እስከ ደመ ዘካርያስ ወልደ በራክዩ። ወዓዲ እስከ ደመ ዮሐንስ መጥምቅ ዘውእቱ ተፈጻሜተ ነቢያት። ወዓዲ ተክዕወ ላዕሌሃ ደመ ሕፃናተ ገሊላ እለ ኢያእመሩ ርስሐተ ዝ ዓለም እስከ ቈሐት ምድር እምደሞሙ ወእስከ ጸዕደወት ዓዲ እምነ ነጸፍጸፈ ሐሊበ እማቲሆሙ። ማቴ፪፥፲፮-፲፰፣፴፫፥፴፮

፴፮ ወእምኵሉሰ ዘየዐቢ ተክዕወ ላዕሌሃ ደመ ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነባቢ ዘይጸርሕ ኀበ አቡሁ እንዘ ይሰክዮሙ ለእለ ከዐውዎ ወያስተሠሪ ሎሙ ኃጣውኢሆሙ ለእለ ይትመጠውዎ በአሚን።

፴፯ ወዓዲ ተክዕወ ላዕሌሃ ደመ እስጢፋኖስ ወደመ ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ በውግረተ እብን።ወደመ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ ዘበሰይፍ ወደመ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ በአጽድፎ እምርእሰ ተድባበ ቤተመቅደስ። ወደመ ስምዖን ወልደ ቀለዮጳ በዲበ መስቀል። ወበዝኒ ኵሉ ዘተክዕወ ደመ ቅዱሳን አኮ ዘኮነ ሙያጤሃ ሠናይ እስመ ዐዘቅተ ደም ይእቲ። ሐዋ፯፥፶፱-፷፣፲፪፥፩

፴፰ ወበርተሎሜዎስኒ ቦአ ሀገረ እልዋኅ ወሰበከ ወንጌለ ጸጋሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወበጽሐ ኀበ ንስማኦፊን ወኒኦኒዶስ አህጉር ዐበይት እለ ሕኑፃን በማዕዶተ ባሕር መልኡ ውስተ ሠቅ ሆፃ ወወደይዎ ውስቴቱ ለንጹሕ ሐዋርያ ወወረውዎ ውስተ ባሕር ወፈጸመ ስምዐ በሰላመ እግዚአብሔር ወእምድኅረዝ አምኑ በስብከቱ።

፴፱ ወኵሎን እንከ አህጉር አሐቲ አሐቲ እምኔሆን፡እምድኅረ አሕመማሁ ለሐዋርያሆን አው ወእምድኅረ ቀተላሁ ለዘሰበከ ሎን የአምና በትምህርቱ ሶበ ተዘከራ መንክራተ እንተ ገብረ በውስቴቶን፡አው ሶበ ርእያ ተአምረ በላዕለ ሥጋሁ ለሐዋርያ ።

፵ ወሀገርነሰ ኢትዮጵያ አኮ ከማሁ ኢያንሶሰዎ እግረ ሐዋርያት ዲቤሃ ወኢተገብረ መንክራተ እግዚእ በውስቴታ አላ አምነቶ በዜና ወተወክፈቶ በድምፅ።ወበእንተዝ ይቤ ነቢይ አዕጻዳተ ኢትዮጵያ ይደነግጻ፣ ይደነግጻ ለአሚን ወኢያገዝፋ ክሳደ ልቦን ለኢአሚን።ይደነግጻ ለሰሚዐ ቃለ እግዚአብሔር ወኢይመይጣ እዝኖን እምአጽምኦ ትእዛዛቲሁ። ይደነግጻ በንስሓ ከመ ይትመየጣ እምሕራማቲሆን ዘትካት። ወይሬውፃ

እንደማይቻለው በነገረው ጊዜ ያ ጐልማሳ ተቆጣ ከመታነቅ ጭንቅ የተነሣ ዓይኑ ልትወጣ እስክትሻ ድረስ ታዴዎስን አነቀው በዚያችም ሰዓት ግመል በመርፌ ቀዳዳ አለፈ ሁለተኛ ሦስተኛም ጊዜ ባለጸጋውን ሰው ለመገሠጽ አለፈ። ከዚህ በኋላ በስብከቱ አመኑ።

፴፭ ኢየሩሳሌምስ ከነቢዩ ከኢሳይያስ ጀምሮ እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ድረስ ሁለተኛም የነቢያት መጨረሻ እስከሆነ እስከ ዮሐንስ ድረስ ብዙ የነቢያት ደም አለባት።ዳግመኛም ከደማቸው መፍሰስ የተነሣ ምድር እስክ ትቀላ ድረስ ከእንደገናም ከእናቶቻው የጡት ወተት ጠብታ የተነሣ ምድር ነጭ እስክትሆን ድረስ የዚህን ዓለም እድፍ የማያወቁ የገሊላ ሕፃናት ደም በርሷ ላይ ፈሰሰ። ማቴ፪፥፲፮-፲፰፣፴፫፥፴፮

፴፮ ከሁሉም የሚከፋው ግን ያፈሰሱትን እየተካሰሰ በማመን ስለሚቀበሉትም ኃጢአታቸውን ይቅር እያለ ወደ አባቱ የሚጮህ የሚናገር የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በርሷ ላይ ፈሰሰ።

፴፯ ዳግመኛም የእስጢፋኖስ ደም የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም ደም በደንጊያ በመወገር ፈሰሰ የዘብዴዎስ ልጅ የያዕቆብ ደም በሰይፍ ፈሰሰ።የጌታችን ወንድም የያዕቆብም ደም ከቤተ መቅደስ ጉልላት በመወርወር የቀለዮጳ ልጅ የስምዖን ደም በእንጨት መስቀል ላይ ፈሰሰ። በዚህ ሁሉ የፈሰሰ የቅዱሳን ደም ያማረ መመለሷ አልሆነም የደም ጉድጓድ ናትና። ሐዋ፯፥፶፱-፷፣፲፪፥፩

፴፰ በርተሎሜዎስም ወደ እልዋህ ሀገር ገብቶ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ወንጌልን አስተማረ በባሕር ወደብ አካባቢ ወደተሠሩ ታላላቆቹ ከተሞች ወደ ንስማአፊንና ወደኒኦኒዶስ ደረሱ። በስልቻ አሸዋ ሞልተው ንጹሁን ሐዋርያ በውስጡ ጨመሩት ወደ ባሕርም ወረወሩት በእግዚአብሔርም ሰላም ምስክርነቱን ፈጸመ ከዚህ በኋላ በስብከቱ አመኑ።

፴፱ እንግዲህ ሀገሮች ሁሉ ከእነርሱም እያንዳንዷ ሐዋርያቶቻቸውን ካሠቃዩ በኋላ የሰበከላቸውንም ከገደሉት በኋላ በውስጣቸው ያደረገውን ተአምራት ባሰቡ ጊዜ ወይም በሐዋርያው በድን ላይ ምልክት ባዩ ጊዜ በትምህርቱ አመኑ ።

፵ ሀገራችን ኢትዮጵያ ግን እንዲህ አይደለም፡ የሐዋርያት እግር በርሷ ላይ አልተመላለሰም የጌታም ተአምራት በውስጧ አልተደረገም በዜና አመነችው በድምፅም ተቀበለችው እንጂ። ስለዚህም ነገር ነቢዩ የኢትዮጵያ አፀዶች ይደነግጣሉ አለ ለማመን ይደነግጣሉ።የልቡናቸውም አንገት ባለማመን አይደነድንም የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ይደነግጣሉ። ጆሮዎቻቸውንም ትእዛዛቱን ከመስማት አይመልሱም ከቀደመው

ኀበ አምልኮቱ ለክርስቶስ::

፴፩ ወበካልዕኒ ይብል አንተ ሰበርከ
ርእሰ ከይሲ በውስተ ማይ::ርእሰ ከይሲ ይተሬ
ጉም በሰቢረ ርእሰ ኀሊናሁ ለሰይጣን::ወአንተ
ቀጥቀጥከ አርእስቲሁ ለከይሲ::ወቅጥቃጤሁሰ
ለርእሰ ከይሲ ከመ ኢይትነሣእ ዳግመ ወከመ
ኢንትመየጥ ንሕነኒ ውስተ አምልኮቱ ነኀልዮ
ከመ ዘሞተ ወኢንዘክሮ ከመ ዘሀሉ::ወወሀብኮ
ሙ ሲሳዮሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ::ዝኒ በእንተ
ቍርባነ ሥጋሁ ወደሙ ለወልደ እግዚአብሔር
ዝ ውእቱ ሲሳየ ጻድቃን ዘለዓለመ ዓለም:: እስ
መ አልቦ ዘይክል ነሢአ ቍርባን ዘእንበለ ይትነ
ዛኀ በማየ ጥምቀት ወይትኀተም በቅብዐ በለሳን::
ወአልቦ ዘይክል ነሢአ ጥምቀት ዘእንበለ ያውግዞ
ለሰይጣን ወይቀጥቅጦ ርእሰ በኃይለ ሃይማኖት::
መዝ፸፫ ፥ ፲፫

፴፪ ወበካልዕኒ ይብል ይምጽኡ
ተናብልት እምግብጽ:ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ
ኀበ እግዚአብሔር::ወዝኒ ትንቢት በእንተ ሢመ
ተ እዴሆሙ ለጳጳሳተ ኢትዮጵያ ከመ እመንበረ
ማርቆስ ውእቱ ይነግር:: መዝ፷፯ ፥ ፴፩

፴፫ ወምክንያተ እምነቶሙሰ ለሰብአ
ኢትዮጵያ ከመዝ ውእቱ እመንግሥተ አርዌ እስ
ከ ርደታ ለንግሥተ አዜብ ኀበ ሰሎሞን ወልደ
ዳዊት ከመ ትስማእ ጥበቢሁ ነበሩ በሕገ አሕዛብ
እንዘ ያመልኩ ምሕራማተ ጣዖት ዘዘዚአሁ::ወአ
መ ተመይጠታ ለንግሥተ አዜብ አምጽአት
ሎሙ ዜና ኦሪት እምኢየሩሳሌም ወነበሩ በሕገ
አይሁድ እምአሚሃ እስከ ምጽአተ ክርስቶስ እንዘ
ይትቀነዩ ለትእዛዘ ሕግ ወሥርዓት ወእንዘ ይፀ
መዱ ለዐቂበ ሰንበታቲሁ ለእግዚአብሔር:: ወበእ
ንተዝ ይቤ ኢሳይያስ ወለእመ ገብኡ እምካልዕ
ሕዝብ ወተቀንዩ ሎቱ ወአፍቀሩ ስመ እግዚአብ
ሔር ወኮንዎ አግብርቲሁ ወአእማቲሁ ለኲሎ
ሙ እለ የዐቅቡ ሰንበታትየ ወኢያረኵሱ ወይት
ዔገሁ በሥርዓትየ አበውኦሙ ውስተ ደብረ
መቅደስየ ወአስተፌሥሖሙ በቤተ ጸሎትየ ወይከ
ውን ኀሩየ ወመሥዋዕትየ ወቍርባንየ ወቤት
የሰ ቤተ ጸሎት ይሰመይ ይቤ እግዚአብሔር
ለኲሉ አሕዛብ:: ወበሆሴዕኒ ይቤ እሬስዮ ሕዝ
ብየ ለዘኢኮነ ሕዝብየ ወእሬስያ ፍቅርትየ ለእንተ
ኢኮነት ፍቅርትየ ወይከውኑ ውሉደ እግዚአ
ብሔር ሕያው በብሔር በኀበ ይቤልዎሙ ኢኮን
ክሙ ውሉደ እግዚአብሔር:: ፩ነገ፲ ፥ ፩-፰
ኢሳ፶፮ ፥ ፰ ሆሴ፪ ፥ ፩

፴፬ ወምክንያተ እምነቶሙሰ በእግዚእ
ኮነ አመ ርደቱ ለሕፅዋ ለህንደኬ ንግሥተ ኢት
ዮጵያ ከመ ይስግድ ለበዓለ ፋሲካ ውስተ ኢየሩ
ሳሌም:: ወእመበ ዘአምነ በውስተ አሕዛብ በሕገ
አይሁድ ወለለበዓለ ፋሲካ ይወርድ ኢየሩሳሌም

ርኩሰታቸው ይመለሱ ዘንድ በንስሐ ይደነግጣ
ሉ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ማምለክም ይሮጣሉ::

፴፩ በሌላም ሥፍራ የእባቡን ራስ
በውኃ ውስጥ ሰበርህ ይላል የእባብን ራስ በውኃ
ውስጥ የሚለው የሰይጣንን አሳብ በመስበር
ይተረጉማል አንተም የእባቡን ራሶች ቀጠቀጥህ
የእባቡ ራስ መቀጥቀጥን ዳግመኛ እንዳይነሣ
እኛም ወደ እርሱ ወደማምለክ እንዳንመለስ ነው
እንደ ሞተ እናስበዋለን እንዳለም አናስታውሰ
ውም::ለኢትዮጵያ ሰዎች ምግባቸውን ሰጠሀቸው
አለ: ይህም ስለ እግዚአብሔር ልጅ የሥጋና
ደሙ ቁርባን የተነገረ ነው:: ለዘላለም የሚኖር
እውነተኛ ምግብ ይህ ነው::በጥምቀት ውኃ ሳይ
ረጭ በበለሳንም ቅባት ሳይታተም ቁርባንን መቀ
በል የሚችል የለምና ሰይጣንንም ሳያወግዘው
በሃይማኖትም ኃይል ራሱን ሳይቀጠቅጥ ጥምቀ
ትን መቀበል የሚችል የለም:: መዝ፸፫ ፥ ፲፫

፴፪ በሌላም ሥፍራ መኳንንት ከግብጽ
ይምጡ::ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር
ትዘረጋለች አለ::ይህም ትንቢት ስለ ኢትዮጵያ
ጳጳሳት ወንበር ከማርቆስ ወንበር እንደሆነ
የተነገረ ነው:: መዝ፷፯ ፥ ፴፩

፴፫ የኢትዮጵያውያን የማመናቸው
ምክንያት እንዲህ ነው::ከዘንዶ መንግሥት ጥበ
ቡን ትሰማ ዘንድ የአዜብ ንግሥት ወደ ዳዊት
ልጅ ወደ ሰሎሞን እስክትወርድ ድረስ ልዩ ልዩ
አማልክትን እያመለኩ በአሕዛብ ልማድ ይኖሩ
ነበር::የአዜብ ንግሥት በምትመለስ ጊዜ ከኢየሩ
ሳሌም የኦሪትን ዜና አመጣችላቸው ከዚያን ጊዜ
ጀምሮ እስከ ክርስቶስ መወለድ ድረስ በሕግ
ትእዛዝና በሥርዓት እየተገዙ የእግዚአብሔርንም
ሰንበቶች ለመጠበቅ እየተጉ በአይሁድ ሕግ ኖሩ
ስለዚህም ነገር ኢሳይያስ ከሌላም ወገን ከተ
መለሱ ተገዙለት የእግዚአብሔርንም ስም ወደዱ
ወንዶችና ሴቶች ባሮችም ሆኑለት ሰንበቶቼን
የሚጠብቁት የማያረክሱአቸውንም በሥርዓቴም
የሚታገሡትን ወደ ተቀደሰው ተራራ አመጣቸ
ዋለሁ:በጸሎት ቤቴም ደስ አሰኛቸዋለሁ መሥዋ
ዕቴና ቁርባኔም የተመረጠ ይሆናል ቤቴም የጸሎ
ት ቤት ይባላል አለ እግዚአብሔር ለሕዝብ ሁሉ
::ሆሴዕም ሕዝቤ ያልሆነውን ሕዝቤ አደርገዋ
ለሁ ወዳጄ ያልነበረችይቱንም ወዳጄ አደርጋታ
ለሁ የእግዚአብሔር ልጆች አይደላችሁም በሚሉ
አቸውም ሀገር የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ
ይሆናሉ:: ፩ነገ፲ ፥ ፩-፰ ኢሳ፶፮ ፥ ፰ ሆሴ፪ ፥ ፩

፴፬ በጌታ የማመናቸውም ምክንያት
የኢትዮጵያ ንግሥት የሕንደኬ ጃንደረባ በፋሲካ
በዓል ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም በሚሄድ ጊዜ
ነው: ከአሕዛብ መካከል በአይሁድ ሕግ ያመነ
ቢኖር የእግዚአብሔር ስም በሚጠራበት ሥፍራ

እስመ ኢይከውኖ ገቢረ ሥርዓተ ፋሲካ በሀገሩ ዘእንበለ ኀበ መካን ዘተሰምየ ስመ እግዚአብሔር።

፴፭ ወበእንተዝ ጽሑፍ ውስተ ወንጌለ ዮሐንስ ዘይብል ወቦ እምውስተ አረሚኒ እለ ዐርጉ ይስግዱ ለበዓል ወሖሩ እሙንቱሂ ኀበ ፊልጶስ ዘቤተ ሳይዳ ዘገሊላ ወይቤልዎ እግ ዚኦ ንፈቅድ ንርአዮ ለኢየሱስ። ወሖረ ፊልጶስ ወነገሮ ለእንድርያስ።ወሖሩ እንድርያስ ወፊሊጶስ ወነገርዎ ለኢየሱስ። ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ በጽሐ ጊዜሁ ከመ ይሰባሕ ወልደ እጓለ እመሕያው። ዝ ብሂል በጽሐ ጊዜሁ ከመ ይእመኑ ብየ አሕዛብ ወይሰብሑኒ። ወበምክን ያተ ዝንቱ ነገር ወረደ ሕጽዋ ለህንደኬ ንግሥተ አትዮጵያ ከመ ይስግድ ለበዓለ አየሩሳሌም በከመ ጽሑፍ ውስተ ግብረ ሐዋርያት። ዮሐ፲፪፥፳፩-፳፯

፴፮ ወነበረ መልአከ እግዚአብሔር ለፊልጶስ ወይቤሎ ተንሥእ ወሑር ጊዜ ቀትር ፍኖተ በድው ዘያወርድ እምኢየሩሳሌም ለጋዛ።ወተንሥአ ወሖረ ወረከበ ብእሴ እምሕዝበ ኢትዮጵያ ሕፅዋ ለህንደኬ ንግሥተ ኢትዮጵያ ወመጋቢሃ ውእቱ ለኵሉ ብሔረ ጋዛ ወሖረ ኢየሩሳሌም ይስግድ። ወእንዘ ይገብእ ነበረ ዲበ ሠረገላሁ ወያነብብ መጽሐፈ ኢሳይያስ ነቢይ ወይቤሎ መንፈስቅዱስ ለፊልጶስ ሑር ትልዎ ለዝንቱ ሠረገላ። ወሮፀ ፊልጶስ ወበጽሐ ወሰምዖ ያነብብ መጽሐፈ ኢሳይያስ ነቢይ ወይቤሎ ፊል ጶስ ተአምርኑ እንከ ዘታነብብ። ወይቤሎ ሕፅው በአይቴ አአምር ለእመ አልቦ ዘመሀረኒ። ወአስ ተብቍዖ ለፊልጶስ ከመ ይዕርግ ወይንበር ኀቡረ ኀቤሁ።

፴፯ ወነገረ መጻሕፍስ ኀበ ያነብብ ከመዝ ይብል ከመ በግዕ ዘኢይነብብ በቅድመ ዘይቀርጾ ከማሁ ኢከሠተ አፉሁ በሕማሙ። ወተንሥአ ኵነኔሁ ወመኑ ይነገር ልደቶ እስመ ተአተተ እምድር ሕይወቱ። ወተመይጠ ኀበ ፊልጶስ ውእቱ ሕፅው ወይቤሎ ብቁዐኒ ንግረኒ በእንተ መኑ ይብል ነቢይ ከመዝ በእንተ ርእ ሱኑ ወሚመ በእንተ ካልዕ።ወከሠተ አፉሁ ፊልጶስ ወአኀዘ ይምሀሮ በእንተ ኢየሱስ ወይፈ ክር ሎቱ በውእቱ መጽሐፍ። ኢሳ፶፫፥፯

፴፰ ወእንዘ የሐውሩ በጽሑ ኀበ ማይ። ወይቤሎ ውእቱ ሕፅው ነዋ ማይ ወመኑ ይከልአኒ ተጠምቆ። ወአዘዘ ያቅሙ ሠረገላሁ ወአቀሙ፡ ወወረዱ ኅቡረ ኀበ ማይ ፊልጶስ ወውእቱ ሕፅው ወአጥመቆ።ወወጺኦሙ እማይ መንፈሰ እግዚአብሔር መሠጦ ለፊልጶስ ወኢር እዮ እንከ ውእቱ ሕፅው ወአተወ ብሔሮ እንዘ ይትፌሣሕ። ወበዜና ዚአሁ አምኑ ሰብአ

ካልሆነ በቀር በሀገሩ ፋሲካን ማክበር አይገባ ውምና ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ነበር።

፴፭ ስለዚህም ነገር በዮሐንስ ወንጌል ከአሕዛብም መካከል በበዓል ሊሰግዱ የወጡ አሉ እነርሱም የገሊላ ዕፃ ወደምትሆን የሳይዳ ሰው ወደሆነ ወደፊልጶስ ሄደው አቤቱ ጌታ ኢየሱስን ልናየው እንወዳለን አሉት ፊልጶስም ሄዶ ለእን ድርያስ ነገረው እንድርያስና ፊልጶስም ሄደው ለኢየሱስ ነገሩት ኢየሱስም መልሶ የሰው ልጅ በክብር የሚገለጥበት ጊዜ ደረሰ አላቸው የሚል ተጽፏል።ይህም ማለት እንግዲህ አሕዛብ ያምኑ ዘንድ ያመሰግኑኝም ዘንድ ጊዜው ደረሰ ማለት ነው።በሐዋርያት ሥራ እንደተጻፈ በዚህም ነገር ምክንያት የኢትዮጵያ ንግሥት የሕንደኬ ጃንደ ረባ ይሰግድ ዘንድ ለበዓል ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። ዮሐ፲፪፥፳፩-፳፯

፴፮ ቀትር በሆነ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ፊልጶስን ተነሥተህ ከኢየሩሳሌም ወደጋዛ በሚወስደው የበረሃ መንገድ ሂድ አለው፡ ተነሥቶም ሄደ ከኢትዮጵያ ሰዎች ወገን የሆነ አንድ ሰው የኢትዮጵያ ንግሥት የሕንደኬ ጃንደ ረባ የጋዛም ሀገር መጋቢያቸው ነበር ወደ ኢየሩ ሳሌምም ሊሰግድ ሄደ ሲመለስም በሠረገላው ተቀምጦ የነቢዩ የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር።መንፈስቅዱስም ፊልጶስን ሂድ ይህን ሠረ ገላ ተከተለው አለው ፊልጶስም ሮጦ ደረሰ የነቢ ዩ የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ ሰማው ፊልጶ ስም የምታነበውን ታውቀዋለህን አለው። ጃንደ ረባውም ያስተማረኝ ሳይኖር ከወዴት አውቀዋ ለሁ አለው ወጥቶም በርሱ ዘንድ አብሮት እንዲቀመጥ ፊልጶስን ለመነው።

፴፯ የሚያነበውም መጽሐፍ ነገር እንዲህ ይል ነበር እንደበግ ሊታረድ መጣ በሚ ሸልተውም ፊት ዝም እንደሚል በግ እንዲሁ በመከራው አፉን አልከፈተም ፍርዱ ተነሣ ልደ ቱን የሚናገር ማን ነው ሕይወቱ ከምድር ተወግዷልና ጃንደረባውም ወደ ፊልጶስ ተመልሶ ንገረኝ ነቢዩ እንደዚህ ስለማን ይናገራል ስለራሱ ነውን ወይስ ስለሌላ አለው ፊልጶስም አፉን ከፍቶ ስለ ኢየሱስ ያስተምረው ዘንድ ያንንም መጽሐፍ ይተረጉምለት ጀመረ። ኢሳ፶፫፥፯

፴፰ ሲሄዱም ወደ ውኃ ደረሱ ጃንደረባውም እነሆ ውኃ እንዳልጠመቅ ማን ይከ ለክለኛል አለ ሠረገላውን እንዲያቆሙ አዘዘ አቆ ሙም፤ ፊልጶስና ጃንደረባውም አብረው ወደ ውኃ ወረዱ አጠመቀውም ከውኃውም ወጥተው የእግዚአብሔር መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው ጃንደ ረባውም ከዚያ ወዲያ አላየውም እየተደሰተም ወደ ሀገሩ ተመለሰ። በእርሱም ዜና የኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ በወንጌለ ጸጋሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ:: ወበእንተ ከዊነ ዐቢየ ክርስትያንሰ ስእኑ ምክን ያተ እስመ ኢኮነ ካህነ ውእቱ ሕፅው ከመ ያጥ ምቆሙ:: ሐዋ፰፥፳፮-፴

፴፱ ወእምድኅረ ብዙኅ ዓመታት ወጕንዱይ አክራም ወፅአ ነጋዲ እምጢሮስ ምስለ ክልዔ ደቂቁ ስመ ፩ ፍሬምናጦስ ወስመ ካልዑ ሲድ ራኮስ::ወእምዝ ደወየ ውእቱ ነጋዲ ወሞተ በው ስተ መርሶ ሐይቀ ባሕር ዘጽንፈ ብሔረ ኢትዮ ጵያ::ወአምጽእዎሙ ለእሙንቱ ደቂቅ እለ አስ ማቲሆሙ ሲድራኮስ ወፍሬምናጦስ ወአቀም ዎሙ ቅድመ ንጉሠ ኢትዮጵያ ወአፍቀርሙ ንጉሥ ወደመርሙ ምስለ ደቂቀ መንግሥት ወነ በሩ እንዘ ያነክሩ ግዕዞሙ ለሰብአ ኢትዮጵያ:: ወይቤሉ እፎኬ አምኑ እስመ ይሬእይዎሙ እንዘ ይገብሩ ምጽላየ ከመ ይስግዱ ለአስማተ ሥላሴ:: ወዲበ አርእስተ አንስቲያሆሙኒ ይሬእዩ ትእምርተ መስቀል ያነክሩ ጥቀ ፈድፋደ ወየአኵትዎ ለእግዚአብሔር እስመ ከፈሎሙ እምነተ ዘእንበለ ስብከት ወተመጥዎ ሃይማኖትኒ ዘእንበለ ሐዋርያ:: በከመ ይቤ ኢሳይያስ ነቢይ ሕዝብ እለ ኢዜነውዎሙ በእንቲአሁ ያአምርዎ ሀለዎ ሙ ወእለሂ ኢሰበውዎ ከመ ይጠይቅዎ:: ወእግ ዚእነሂ ይቤ በወንጌል ሶበ ርኢከኒሁ አመንከኒ ቶማስ::ብፁዓንሰ እንዘ እለ ኢይሬእዩኒ የአምኑ:: ዮሐ፳፥፳፱

፵ ንትመየጥኬ ኀበ ጥንተ ነገሮሙ ለፍሬምናጦስ ወለሲድራኮስ ወነበሩ ውስተ ጽር ሐ ንጉሥ አምጣነ ሕያው ውእቱ ነጋሢ::ወሶበ አልጸቀ ለመዊት ረሰዮሙ አግዓዝያነ ወአብሖሙ ይሑሩ ኀበ ፈቀዱ::ወሲድራኮስ አተወ ኀበ ሀገሩ ጢሮስ ወፍሬምናጦስኒ ሖረ ኀበ ሊቀጳጳሳት ዘእለስክንድርያ ከመ ይኅሥሥ ምክንያተ ድኅነ ቶሙ ለሰብአ ኢትዮጵያ::ወዜነወ ፍጹመ እምነ ቶሙ ዘእንበለ ትምህርተ ሐዋርያት:: ወአንከረ ሊቀጳጳሳት በእንተ ዘኮነ እምነቶሙ ዘእንበለ ስብከት ወአእኰቶ ለእግዚአብሔር:: ወይቤሎ ለፍሬምናጦስ አንተ ኩኖሙ ኖላዌ እስመ ኪያከ አልሀቀ እግዚአብሔር ወተመየጥ ኀቤሆሙ:: ወአንበረ እዴሁ ጸሎተ ተክሬዝ ዘሢመተ መጥሮ ቦሊለጥ ዘውእቱ ጳጳስ::

፵፩ ወጽአ ፍሬምናጦስ ብሔረ አግዓዚ ወአጥመቆሙ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈ ስቅዱስ::ወሤመ ሎሙ ኤጲስቆጳሳተ ቀሳውስተ ወዲያቆናተ:: ውእቶሙኒ አፍቀርዎ ከመ አቡሆ ሙ ወአክበርዎ ከመ አምላኮሙ ወሰመይዎ አባ ሰላማ እስመ ሰላመ አምጽአ ሎሙ:: ወፀአቱሰ ኮነ በመንግሥተ አብርሃ ወአጽብሃ እለተወከፍዋ ለትምህርተ ጽድቅ ከመ ምድር ጽምእት እንተ ትሰቲ ዝናመ ተፈሢሓ::

፵፪ ወእምድኅረ ጕንዱይ መዋዕል

ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ የጸጋ ወንጌል አመኑ:: ዐቢየ ክርስቲያን ስለመሆን ግን ምክንያት አላገ ኙም ጃንደረባው ያጠምቃቸው ዘንድ ካህን አይ ደለም:: ሐዋ፰፥፳፮-፴

፴፱ ከብዙ ዓመታትና ከብዙ ክረምቶች በኋላ አንድ ነጋዴ ከሁለት ልጆች ጋር ከጢሮስ መጣ የአንዱ ስሙ ፍሬምናጦስ ነው የሁለተኛ ውም ስሙ ሲያድራኮስ ነው፡ ከዚህ በኋላ ያ ነጋ ዴ በኢትዮጵያ ባሕር ዳርቻ የባሕር ወደብ አካባቢ ታምሞ ሞተ ስማቸው ፍሬምናጦስና ሲ ድራኮስ የተባለ እነዚያን ብላቴኖች አመጡአ ቸው በኢትዮጵያም ንጉሥ ፊት አቆሙአቸው ንጉሥም ወደዳቸው ከመንግሥት ልጆችም ጋር ቆጠራቸው::እነርሱም የኢትዮጵያን ሰዎች ባህል እያደነቁ ተቀመጡ እንደምን አመኑ ይሉም ነበር ለሥላሴ ስም እንዲሰግዱ መጸለያ ሲሠሩ አይ ተዋቸዋልና በሴቶቻቸውም ራስ ላይ የመስቀል ምልክት እያዩ እጅግ ያደንቁ ነበር እግዚአ ብሔርንም ያመሰግኑታል ያለስብከት እምነትን አድሏቸዋልና ያለሐዋርያም ሃይማኖትን መቀበ ልም ነቢዩ ኢሳይያስ ስለርሱ ያልነገሩአቸው ሕዝቦች ያውቁት ዘንድ አላቸው ያላስተዋሉትም ፈጽመው ይረዱታል አለ::ጌታችንም በወንጌል ቶማስ ስላየኸኝ አመንክብኝ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለ:: ዮሐ፳፥፳፱

፵ ወደ ፍሬምናጦስና ሲድራኮስ ታሪክ መጀመሪያ እንመለስ:: ንጉሡ በሕይወት በቆየበት ጊዜ በንጉሥ ቤት ተቀመጡ ለሞት በተቃረበበት ጊዜ አርነት አወጣቸው ወደ ወደ ዱትም እንዲሄዱ አሰናበታቸው ሲድራክስ ወደ ሀገሩ ወደ ጢሮስ ተመለሰ ፍሬምናጦስም ለኢት ዮጵያ ሰዎች ለመዳናቸው ምክንያት ይፈልግ ዘንድ ወደ እስክንድርያ ሊቀጳጳሳት ሄደ::ያለ ሐ ዋርያት ትምህርት ስለ ሆነ ፍጹም እምነታቸው ነገረው ሊቀጳጳሳቱም ያለ ስብከት ስለሆነ እምነ ታቸው አደነቀ እግዚአብሔርንም አመሰገኑት:: ፍሬምናጦስንም እግዚአብሔር አንተን ከፍ ከፍ አድርጎሀልና አንተ እረኛ ሁንላቸው ወደነርሱ ም ተመለስ አለው::ሊቀጳጳሳቱም እጁን በፍሬም ናጦስ ራስ ላይ አኖረ በርሱም ላይ መጥሪብሊስ የተባለ የጳጳስን ሹመት የተክሪዝ ጸሎት ጸለየ::

፵፩ ፍሬምናጦስም ወደ ብሔረ አግዓዚ ተመለሰ በአብና በወልድ በመንፈስቅዱስም ስም አጠመቀው ኤጲስቆጶሳትንና ቀሳውስትን ዲያቆና ትንም ሾመላቸው እነርሱም እንደአባታቸው ወደ ዱት እንደ አምላካቸውም አከበሩት ሰላምንም አምጥቶላቸዋልና አባ ሰላማ አሉት::የመጣው ደስ ብሏት ዝናምን እንደምትጠጣ የተጠማች ምድር የጽድቅ ትምህርትን በተቀበሉአት በአብር ሃና አጽብሃ መንግሥት ነው::

፵፪ ከጥቂት ጊዜ ከብዙም ክረምቶች

ወብዙኀ ክረምት ወእምድኅረ ኀለፉ ብዙኃን ነገሥተ አክሱም መጽኡ ቅዱሳነ ሮም ምስለ ንጉሦሙ ወመሳፍንቲሆሙ ወመኳንንቲሆሙ ምስለ ካህናቲሆሙ ወመሥዋዕቲሆሙ ምስለ ንዋየ ቅድሳቲሆሙ ወመጻሕፍቲሆሙ ወምስለ ሕዝቢሆሙ:: ወፀአቶሙሰ ኮነ በመንግሥተ አልአሚዳ ወልደ ሰልአደባ:: ደንገፀት ምድር እምፀአቶሙ ወተከውሰት አድያመ ኢትዮጵያ እስመ መሰሉሙ ዘወፅኡ ለወሪሰ ሀገሮሙ ወለአንሥአ መራድ ላዕሌሆሙ:: ወውእቶሙሰ አርአዩ ኃይለ ሃይማኖቶሙ:: ቦ እለ አፍለሱ አድባረ::ወቦ እለ አፍለሱ ባሕረ::ወቦ እለ ዘርእዎ ለሥርናይ በነግህ ወወደይዎ ውስተ ምክያድ በጊዜ ሠርክ ምክያዱኒ ዲበ ዕፀ ገራይ እንዘ ቈጽለ ዕፀው ኢይትነገፍ ወአባዕሪሁኑ ኢይ ጸድፉ ወፍሬ ሥርናይሰ ወረደ ወኮነ ክምረ ውስተ ዐውድ ወኀሠሩሰ ተገድፈ ውስተ ቈጽለ ኦም:: ሐረጽዎ ለሥርናይ ወበጽሐ ለመሥዋዕተ ሠርክ::

፺፫ ወቦ እለ ተከሉ ዕፀ አውልዕ በጊዜ ነግህ ዲበ ኰኵሕ ልሙጽ በቄለ በጊዜሃ ወኮነ ዕፀ ዐቢየ የብሰ ጕንዱ በፈቃደ እግዚአብሔር ሠፀርዎ ወአንደድዎ ወዐቄሩ ፍሕሞ በልብስ ረቂቅ ወበጽሐ ለዕጣን ሠርክ::ወቦ እለ አስተናገሩ ምውተ እምድኅረ ሞተ::ወቦ እለ ዐቄሩ ማየ በመንፌ ወኢተክዕወ ማዩ ወአእተውዎ ለመልእክተ ቤተክርስቲያን ወለሥርዓተ ቍርባን ::

፺፬ ወቦ ዘተገንዘ እምኔሆሙ በእደ መላእክት ደነነ ዓምደ እብን ዐቢይ ዘይትሌዓልኑት እምነ ጸድፍ ዐቢይ ወተመጠወ ሥጋሁ እማዕዶተ ፈለግ ወቆመ ርቱዐ ወኮነ በድነ ቅዱስ ውስተ ድማሁ ለዓምደ እብን እስከ ዮም:: ወአሠረ ግንዘቱኒ ናሁ ያስተርኢ ውስተ ኰኵሕ ልሙጽ ከመ ዘተሥእለ በዕደ ኬንያ ጠቢብ:: ወቦ እምኔሆሙ እለ አብርሃ ዐሥሩ አጻብዐ እደዊሆሙ ወዐሥሩ አጻብዓ እገሪሆሙ ከመ ማኅቶተ መብረቅ እንዘ ሀለዉ ቀዊሞሙ ጊዜ ጸሎት:: ወቦ እምኔሆሙ እለ ተከብቱ እምገጸ ሞት ወድኅኑ በጸጋ እግዚአብሔር::

፺፭ ወቦ እምኔሆሙ ዘቀደመ ወጊአ ውስተ ሀገርነ ወተመይጠ ኀቤሆሙ ወዜነውምሙ ዜና ኂሩታ ለኢትዮጵያ ዘከመ አምነት በክርስቶስ ዘእንበለ ስብከተ ሐዋርያት:: ወእምዝ ነደ አባላቲሆሙ ለእሙንቱ ቅዱሳን በላህበ ሃይማኖቱ ለክርስቶስ ወወፅኡ ውስተ ሀገርነ ምስለ ኵሉ ቍስቋሶሙ::ተቀደሰት ምድር በኪደተ እግሮሙ ወተሐደሰ አዕጻዳቲሃ በነሶሳዎሙ ወተክዕወ ውስተ አድያሚሃ መዓዛ ቃሎሙ:: ወእመንግሥተ እልአሚዳ ወልደ ሰልአዶባ እስከ መንግሥተ ካሌብ ወልደ ታዜና ነበሩ ውስተ ቤተቀጢን አማኅቢሮሙ እንበለ ፍልጠት እንዘ

በኋላ ብዙም የአክሱም ነገሥታት ካለፉ በኋ የሮም ቅዱሳን ከንጉሣቸውና ከመሳፍንቶቻቸወ ከመካንንቶቻቸው ከካህናቶቻቸውና ከመሠዊያ ዎቻቸው ከወገኖቻቸውም ሁሉ ጋር መጡ:: መምጣታቸውም በሰልአደባ ልጅ በአልአሚዳ መንግሥት ነው በመጡም ጊዜ ምድር ደነገጠች የኢትዮጵያ አውራጃዎች ተናወጹ ሀገራቸውን ለመውረስ የመጡ በላያቸውም ላይ ሽፍታ ለማስነሣት መስሎአቸዋልና:: እነርሱ ግን የሃይማኖታቸውን ኃይል አሳዩ ተራሮችን ያፈለሱ አሉ ባሕርን የብስ ያደረጉም አሉ ስንዴውን ጠዋት ዘርተው በሠርክ ወደ ወፍጮ የጨመሩ አሉ ወፍጮውም የግንዱ ቅጠል ላይ ረግፎ በግራር ዛፍ ላይ ነው በሬዎቹም አይወድቁም የስንዴው ፍሬ ወረደ በዓውድማም ተከመረ ገለባውም በዛፉ ቅጠል ላይ ቀረ ስንዴውን ፈጩት ለሠርክ መሥዋዕትም ደረሰ::

፺፫ ጠዋት የወይራ ችግኝ በጠፍጣፋ አለት ላይ የተከሉ አሉ፡ ያን ጊዜ በቀለ ታላቅ ዛፍም ሆነ በእግዚአብሔር ፈቃድ ግንዱ ደረቀ ቆርጠውም አነደዱት ፍሕሙን በስስ ልብሰ ቋጠሩት ለሠርክ ዕጣንም ደረሰ:: ከሞት በኋላ ሙት ያናገሩ አሉ፡ ውኃ በወንፊት የቋጠሩ አሉ ውኃውም አልፈሰሰም ለቤተክርስቲያንም አገልግሎት ለቁርባንም ሥርዓት አስገቡት::

፺፬ ከእነርሱም መካከል በመላእክት እጅ የተገነዘ አለ ርዝመቱ ከታላቅ ገደል ይልቅ ከፍ የሚል የደንጊያ ምሶሶ አጐነበሰ ከወንዝ ማዶም ሥጋውን ተቀበለ የቅዱሱም በድን እስከዛሬ ድረስ የድንጊያው ምሰሶ አናት ላይ ቀጥ ብሎ ቆመ የግንዘቱም ምልክት እነሆ በጥበበኛ ሰአሊ እጅ እንደተሣለ ሆኖ በጠፍጣፋ አለት ላይ ይታያል::ከእነርሱም መካከል አሥሩ የእጆቻቸው ጣቶች አሥሩም የእግሮቻቸው ጣቶች በጸሎት ጊዜ ቆመው ሳሉ እንደ መብረቅ ብርሃን ያበሩ አሉ. ከእነርሱም መካከል ከሞት ፊት የተሠወሩ በእግዚአብሔርም ጸጋ የዳኑ አሉ::

፺፭ ከእነርሱም መካከል ወደ ሀገራችን በመምጣት የቀደመ ወደነርሱም ተመልሶ ያለ ሐዋርያት ስብከት በክርስቶስ እንዳመነች የኢትዮጵያን በጎነት ዜናዋን የነገራቸው አለ፡ ከዚህም በኋላ የእነዚህ ቅዱሳን ሰውነታቸው በክርስቶስ የሃይማኖት ወላፈን ተቃጠለ ከጓዛቸውም ሁሉ ጋር ወደ ሀገራችን መጡ በእግራቸው መረገጥ ምድር ተቀደሰች በመመላለሳቸውም አፀዶቿ ታደሱ የቃላቸው መዓዛ በአውራጃዎቿ ፈሰሰ እነርሱም ከሰልአዶባ ልጅ ከአልአሚዳ መንግሥት እስከ ታዜና ልጅ እስከ ካሌብ መንግሥት ድረስ በሰማይ እንደሚያበሩ ከዋክብት የአበባቸ

ያሬእዩ ስነ ጽድቆሙ ከመ ከዋክብት ብሩሀት
ዘያንበለብሉ በገጸ ሰማይ ወከመ ዕፀወ ገነት
ምዑዛን ዘዘዚአሁ ሥነ ጽጌሆሙ ወዘዚአሁ አስ
ካለ ፍሬሆሙ:: ወከመ አእባነ ህንደኬ ጽዱላን
ዘዘዚአሁ ሥነ ሞገሶሙ ወዘዘዚአሁ ኅበሪሆሙ::
ወከመ አፈዋተ ርጌ ጽዑጥ ዘይትዐቀብ በቀርነ
ቅብዕ ዘጽዮን::ከመ አዕማደ ባሕርይ እለ ስፉራን
ዲበ እብነ ሰንፔር ወከመ እብነ ጳዝዮን ዘአስተ
ጣበቅዕዎ በወርቅ ጽሩይ ዘእምፓሩዬም::ከንዋ
ሰርጕ ለምድረ አክሱም ከመ ባዝግና ወርቅ ዲበ
ርእሰ ነገሥት ወከመ ሕልቀተ ክብር ዘውስተ
አጻብዒሆሙ ለመሳፍንት ምድር::ወአወፈይዋ
መጻሕፍተ ሕጎሙ ወሥርዐቶሙ ወአስተጻንዕዋ
በትእዛዘ ትምህርቶሙ ለሐዋርያተ ክርስቶስ::

፵፮ ወመክብበ መጻሕፍቲሃሰ ዘብሉይ
ተዐልዋ እምዕብራይስጢ ኀበ ግዕዝ በመዋዕሊሃ
ለንግሥተ አዜብ እንተ ሖወጸቶ ለሰሎሞን:: ወበ
እንተዝ ኮነ ጽሩየ ፍካሬሆሙ ለመጻሕፍተ ነቢ
ያት ዘውስተ ብሔረ አግዓዚ እስመ በሕገ አይሁ
ድ ነበሩ እምድቅመ ልደተ ክርስቶስ::

፵፯ ወእመሰኬ አዕለውም እምድኅረ
ልደተ ክርስቶስ እሜጡ ሰቃልያን ቃለ ጽድቅ
ውስተ ስምዐ ሐሰት:: ወከመ ተዐልዋ መጻሕ
ፍተ ነቢያት እምዕብራይስጢ ኀበ ግዕዝ ትረክብ
ትእምርተ በውስተ መጽሐፈ ነገሥት ዘይብል
ትርጓሜ ነገረ ዕብራይስጢ ኀበ ግዕዝ ኤሎሄ
ብሂል አምላክ፣ አዶናይ ብሂል እግዚእ፣ ጸባዖት
ብሂል ዘኃይላት::

፵፰ ወመጻሕፍቲሃሰ ለሐዲስ ለምድርነ
ኢትዮጵያ ተዐልዋ እምሮማይስጢ ኀበ ግዕዝ
እምቅድመ ያስተርኢ ሃይማኖተ ንስጥሮስ ወእም
ቅድመ ይትፈጠር ሃይማኖተ ልዮን ወእምቅድመ
ይትጋብኡ ማኅበረ ከለባት ዘውእቶሙ ኤጲስቆ
ጶሳት ዘኬልቄዶን::ወበእንተዝ ኮነ ፍካሬ መጻሕ
ፍቲሃ ለብሔረ አግዓዚ ዘብሉይኒ ዘሐዲስኒ
ንጡፍ ከመ ወርቅ ወፍቱን ከመ ብሩር ወንጹሕ
ከመ ሐሊብ ዘአልበ ቱሳሔ::

፵፱ ወእመኒ ይወርድ ንጉሠ ኢትዮጵያ
ውስተ ኢየሩሳሌም ወይነግድ ንጉሠ ሮሜኒ
እምቍስጥንጥንያ ወየሐውር ንጉሠ ኢትዮጵያ
ምስለ ሊቀጳጳሳት ዘእለስክንድርያ:: ወይመጽእ
ንጉሠ ሮሜሂ ምስለ ሊቀጳጳሳት ዘቍስጥንጥንያ
ወይትራከቡ በቤተ አባ ሲኖዳ:: ወይብል ንጉሠ
ሮሜ ምስለ ሊቀጳጳሳት ዘቍስጥንጥንያ ዚአነ
ሃይማኖት ይኄይስ::ወይብል ካዕበ ንጉሠ ኢት
ዮጵያ ምስለ ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ እንቲአነ
ሃይማኖት ትኄይስ ወትሤኒ::

ውም ማማር ለየራሳቸው የሆነ የሚጣፍጥ ሽታ
ለየራሳቸውም የሆነ ፍሬ እንዳላቸው የገነት ዛፎ
ች ጸዳላቸው የየራሳቸው ኅብራቸውም ለየራሳቸ
ው የሆነ እንደሚያበሩ የሕንድ ደንጊያዎች በጽዮ
ን የዘይት ቀንድ እንደሚጠበቅ የጣፈጠ ሽቱ በሰ
ንፔር ደንጊያ ላይ እንደተቀመጡ የዕንቍ ምሰ
ሶዎች ከፓሩሄም በተገኘ የጠራ ወርቅ እንዳያ
ያዙት የጳዝዮን ደንጊያ የጽድቃቸውን ጸዳል
እያሳዩ ያለመለየት በአንድነት በቤተ ቀጢን ኖሩ፡
በሙሽሪት አንገት ላይ እንዳለ የወርቅ ማርዳ
በሙሽራም ራስ ላይ እንደሚሆን የሥርግ አክሊ
ል በነገሥታት ራስ ላይ እንደሚቀመጥ የዕንቍ
ዘውድ በምድር ገዢዎችም ጣቶች ውስጥ እንደ
ሚታሠር የክብር ቀለበት ለአክሱም ምድር ጌጥ
ሆኗት የሕጋቸውንና የሥርዓታቸውን መጻሕ
ፍት ሰጡአት በክርስቶስ ሐዋርያት ትምህር
ትም አጸኑአት::

፵፮ የብሉይ የመጻሕፍቷ ዋንኛው
ሰሎሞንን በጐበኘችው በአዜብ ንግሥት ዘመን
ከዕብራይስጥ ወደ ግዕዝ ተተረጐመ:: ስለዚህም
ነገር በብሔረ አግዐዚ ውስጥ ያሉ የነቢያት መጻ
ሕፍት ትርጉም የጠራ ሆነ ከክርስቶስ ልደት
አስቀድሞ በአይሁድ ሕግ ይኖሩ ነበርና::

፵፯ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ተርጉመ
ውትስ ቢሆን ሰቃዮች የጽድቁን ቃል ወደ ሐሰት
ምስክርነት በለወጡት ነበር::የነቢያት መጻሕፍት
ከዕብራይስጥ ወደ ግዕዝ እንደተተረጐመ መልእ
ክቱን የዕብራይስጡን ቃል ሳይተረጉም በግዕዝ
ተጽፎ ታገኘዋለህ ኤሎሄ ማለት አምላክ ማለት
ነው፣ አዶናይ ማለት ጌታ፣ ማለት ነው ጸባዖት
ማለት አቸናፊ ማለት ነው::

፵፰ የአዲስ ኪዳን መጻሐፍት የንስጥ
ሮስ ሃይማኖት ሳይገለጥ የልዮንም ሃይማኖት
ሳይፈጠር የውሾች ማኅበርተኞች የሆኑ የኬል
ቄዶን ኤጲስቆጶሳት ሳይሰባሰቡ አስቀድሞ ለሀገራ
ችን ለኢትዮጵያ ከሮማይስጥ ወደ ግዕዝ ተተረ
ጐመ::ስለዚህም የብሔረ አግዓዚ መጻሕፍት
ትርጉም የብሉይም የአዲሱም እንደወርቅ የጠ
ራ እንደ ብርም የተፈተነ ውኃ አዥራር እንደ
ሌለበትም ወተት ንፁህ ሆነ::

፵፱ የኢትዮጵያ ንጉሥ ወደ ኢየሩሳ
ሌም ቢሄድ የሮሜም ንጉሥ ወደ ቁስጥንጥንያ
ይሄዳል::የኢትዮጵያ ንጉሥ ከእስክንድርያ ሊቀጳ
ጳሳት ጋር ቢሄድ የሮሜም ንጉሥ ከቁጥንጥን
ያው ሊቀጳጳሳት ጋር ይመጣል በአባ ሲኖዳም
ቤት ይገናኛሉ የሮሜ ንጉሥ ከቁስጥንጥንያው
ሊቀጳጳሳት ጋር የእኛ ሃይማኖት ይሻላል ይላል
ዳግመኛም የኢትዮጵያ ንጉሥ ከእስክንድርያ
ሊቀ ጳጳሳት ጋር የእኛ ሃይማኖት ትሻላለች ያማ
ረችም ናት ይላል ::

፶ አንትሙሰ ሰብአ ሮሜ ገበርክሙ ፍልጠተ ማእከለ ትስብእቱ ወመለኮቱ:: ከፈልክምዎ ለዘኢይትከፈል ወአንቃዕክምዎ ለዘኢይትሌለይ:: ወእምዝ ይነውኀ ጋዕዝ በእንተ ተስናነ ነገርኒ ወበቃለ መጻሕፍትኒ እስመ ትውፊተ መጻሕፍቲሆሙኒ ዘብሉይ ኮነ አመ ጻአቶሙ ለቅዱሳነ ሮሜ::ወእምዝ ይመውዕዎሙ መምህራነ ሮም እስመ መጻሕፍቲሆሙ ኀየለ እመጻሕፍተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም:: ወበእንተዝ ይቤ ኢሳይያስ ወእምዝ ይከውኖሙ ኀፍረተ ወያበዝኑ ካሕደ ወይብሉ ዲበ ዘወረደ መንፈስቅዱስ ዲበ ምሥዋዒሁ እምሊቃነ ጳጳሳተ ዚአነ ወእምሊቃነ ጳጳሳተ ዚአክሙ ይኩን መዊዕ::

፶፩ ወእምዝ ይቄድስ ሊቀጳጳሳተ ሮሜ ውስተ ፩ ምሥዋዕ ወሊቀ ጳጳሳተ እስክንድርያኒ ውስተ ፩ ምሥዋዕ:በቅድመ መለካውያን ወያዕቆባውያን በቅድመ አይሁድ ወተንባላት ወአረሚ:: ወእምዝ ይወርድ ገሀደ ውስተ ምሥዋዒሁ ለሊቀጳጳሳተ እለስክንድርያ መንፈስቅዱስ በርእየተ ርግብ ጸዓዳ ገበዋቲሁ ዘሐመልማለ ወርቅ: ወክነፊሁ ዘመዓዝረ ፀሐይ ወዘነቡ ዘአዝፋረ መባርቅት:: ከርሡ ወእንግድዓሁ ዘዕንቍ ኢያስጲድ ወሰርዲኖ::ክሳዱ ከመ ብርሃን ዘለንጳስ ገጹ ዘሜሎስ ወአዕይንቲሁ ዘጳዝዮን ወዲበ ርእሱ ትእምርተ መስቀል ዘማዕተበ ብርሃን ወዲበ ውእቱ ማዕተበ ብርሃን ሥዕለ ገጸ በግዑ ዘይጸርሕ ወይብል አነ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ናዝራዊ አምላኮሙ ለናዝራውያን:: ወእምዝ ይትፌሣሕ ንጉሠ ኢትዮጵያ ወይዌውዕ በቃለ ይባቤ ምስለ ሕዝቢሁ::ወሊቀ ጳጳሳተ እለስክድርያኒ ምስለ ኤጲስቆጶሳተ ግብጽ ወምስለ ኵሉ መምህራኒሆሙ ይትፌሥሑ ቦሙ ለሰብአ ኢትዮጵያ እስመ በቃለ መጻሕፍቲሆሙ ኮነ ሥምረተ እግዚአብሔር:: ራእ፳፩÷፲፰

፶፪ በእንተዝ ይቤ ኢሳይያስ ወይትሜክሑ ግብጽ በኢትዮጵያ:: እስመ ሰብአ ግብጽ ወኢትዮጵያ ሱቱፋነ ሃይማኖት ወኅቡራነ ክህነት እሙንቱ::ወእምዝ ይለብሱ ኀፍረተ ወኀሣረ ሰብአ ሮሜ ምስለ ሊቀ ጳጳሳቲሆሙ ወምስለ ንጉሦሙ::ምስለ ኤጲስቆጳሳቲሆሙ ወምስለ ኵሉ ተዐይነ ማኅበሮሙ::ወበእንተዝ ይቤ ደዊት ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ:: ወጸላዕቱሂ ሐመደ ይቀምሑ::አማንኬ ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ:: ወጸላዕቱሂ ሐመደ ይቀምሑ:: አማንኬ ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ በእንተ ዘከፈሎሙ መዊዐ በቃለ መጻሕፍት ከመ ያስተኀፍርዎሙ ለዐበይተ ሮሜ:: መዝ፷፯÷፴

፶፫ አማንኬ ዘይቤ ወጸላዕቱሂ ሐመደ ይቀምሑ:: ዝኒ በእንተ ኀሣረ ስብከቶሙ ለመለካውያን እስመ መለካውያን ብሂል ሰብአ ንጉሥ

፶ እናንተ የሮሜ ሰዎች በትስብእትና በመለኮቱ መካከል መለያየትን አደረጋችሁ የማይከፈለውን ከፈላችሁ የማይለይ እርሱን ከፈላችሁት::ከዚህም በኋላ ስለነገር ክርክርም በመጻሕፍት ቃል ክርክር ይበዛል የብሉይ መጻሕፍቶቻቸው ትውፊት ንግሥተ አዜብ ከኢየሩሳሌም በወጣች ጊዜ ነውና::የአዲስ መጻሕፍቶቻቸውም ትውፊ ት በሮሜ ቅዱሳን መምጣት ጊዜ ነውና::ከዚህም በኋላ የኢትዮጵያ መምህራን የሮሜ መምህራንን ያቸንፏቸዋል መጻሕፍቶቻቸው ከዓለም ዳርቻ ዎች ሁሉ መጻሕፍት ይልቅ በርትተዋልና ስለዚ ህም ነገር ኢሳይያስ ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ መጻሕፍት ያመጣሉ አለ::ከዚህም በኋላ አፍረት ይሆንባቸዋል ማቸነፍ ከእኛ ሊቃነ ጳጳሳትና ከእናንተ ሊቃነ ጳጳሳት በመሠዊያው ላይ መንፈስ ቅዱስ በወረደበት ይሁን ብለው ክህደትን ያበዛሉ::

፶፩ ከዚህም በኋላ የሮሜ ሊቀ ጳጳሳት በአንድ መሠዊያ የእስክንድርያውም ሊቀ ጳጳሳት በአንዱ መሠዊያ በመለካውያንና በያዕቆባውያን በአይሁድና በተንባላት በአሕዛብም ፊት ይቀድሳል፤ከዚህም በኋላ ጉኖቹ የወርቅ ሐመልማል ክንፎቹም የፀሐይ ወጋገን ጭራው የመብረቆች ብልጭታ ሆዱና ደረቱ የኢያስጲድ ዕንቍና የሰርዲኖ አንገቱም የብርሃን ላንቃ መልኩ የሚያንጸባርቅ ዓይኖቹም የጳዝዮን በራሱም ላይ ትእምርተ መስቀል በብርሃን ማዕተቡም ላይ እኔ የናዝራውያን አምላካቸው ናዝራዊው ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ ብሎ የሚጮህ የበጉ መልክ ሥዕል ባለበት ነጭ ርግብ አምሳል መንፈስቅዱስ በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት መሠዊያ ላይ ይወርዳል::ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ንጉሥ ይደሰታል ከወገኖቹም ጋር በእልልታ ቃል ይጮሀል የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳትም ከግብጽ ኤጲስቆጳሳትና ከመምህራኖቻቸው ሁሉ ጋር በኢትዮጵያ ሰዎች ደስ ይሰኙባቸዋል በመጽሐፎቻቸው ቃል የእግዚአ ብሔር ውድ ሆኗልና:: ራእ፳፩÷፲፰

፶፪ ስለዚህም ነገር ኢሳይያስ ግብጻውያን በኢትዮጵያውያን ይመካሉ አለ፡ የግብጽና የኢትዮጵያ ሰዎች በሃይማኖት አንድ በክህነትም የሚተባበሩ ናቸውና ከዚህ በኋላ የሮም ሰዎች ከሊቀ ጳጳሳታቸውና ከንጉሣቸው ጋር ከኤጲስቆጳሳቶቻቸውና በጉባኤያቸው ከተሰበሰቡት ሁሉ ጋር አፍረትንና ኀሣርን ይለብሳሉ ስለዚህም ዳዊት ኢትዮጵያውያን በፊቱ ይገዛሉ፡ጠላቶቹም አመድን ይቅማሉ አለ::በእውነትም የሮሜን ታላላቆች በመጻሕፍት ቃል ያሳፍሩአቸው ዘንድ ማቸነፍን አድሏቸዋና ኢትዮጵያውን በፊቱ ይገዛሉ:: መዝ፷፯÷፴

፶፫ በእውነትም ጠላቶቹም አመድን ይቅማሉ አለ ይህም ስለመለካውያን የስብከታቸው ጉስቁልና ነው::መለካውያን ማለት

ብሂል ወእኮ ሰብአ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እስመ ኀበ ሠምረ መርቅያን ንጉሥ ኮነ ተመይጦቶሙ በእንተ ፍርሀተ ኵነኔ ወስደት፡፡ ወበእንተዝ ተሰምዩ ንጉሣውያን ወአኮ ክርስቶሳውያን፡ እስመ መላኪ ብሂል በልሳነ ዐረብ፡ እስመ ስመ ሃይማኖቶሙ ያዐውቅ ካሕዶሙ እስመ ማዕተብ ትእምርተ መስቀል አድሰው ለንጉሥ እምያድልው ለእግዚአብሔር፡፡

፶፬ ንትመየጥኬ ኀበ በነገረ ዜናሆሙ ለንጉሠ ሮም ወለሊቀ ጳጳሳተ ቍስጥንጥንያ ወለኵሉ ማኅበረ ተዓይኒሆሙ ዘከመ ይኔስሑ ወይትመየጡ እምሃይማኖቶሙ ርኵስት ሶበ ይሬእዩ ርደተ መንፈስቅዱስ ዲበ ምሥዋዒሁ ለሊቀጳጳሳተ እለስክንድርያ ወይዌርዉ መጻሕፍቲሆሙ ውስተ ቀላየ ባሕር ዘውእቱ መጻሕፍተ ሐሰት ዘአስተንፈሰ ሰይጣን ውስተ አፉሆሙ፡፡ ወዓዲ ይረግምዎ ለልዮን አቡሆሙ ዘመሀርሙ ዕልወተ፡፡ወእምዝ ይከውን ፍቅር ወስንዕ ወሰላም ማእከለ ንጉሠ ኢትዮጵያ ወማእከለ ንጉሠ ሮም ዘውእቱ ወልደ አንበሳ፡፡ወይገብእ ምኵናነ ኢየሩሳሌም ኀበ ንጉሠ ሮም ወምኵናነ ምሥር ወግብጽ ኀበ ንጉሠ ኢትዮጵያ፡፡ ወእምዝ የአትዉ ለለ አህጉሪሆሙ በሰላም በከመ ነገረ አባ ሲኖዳ ርእሰ መነኮሳት ወአበ ባሕታውያን፡፡

፶፭ ወለብሂለ ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ ወጸላዕቱሂ ሐመደ ይቀምሑ ካዕበ ዓዲ ቦቱ ትርጓሜ እስመ ፈላስያነ ኢትዮጵያ እለ ይወርዱ ኢየሩሳሌም ይገንዩ ወያስተበርኩ ውስተ ቤተልሔም ኀበ ተወልደ፡፡ ወይገንዩ ወይሰግዱ ወይትሐፀቡ ውስተ ፈለገ ዮርዳኖስ ኀበ ተጠምቀ፡፡ ይገንዩ ወይሰግዱ ውስተ መካነ ቀራንዮ ኀበ ተሰቅለ፡፡ ወካዕበ ዓዲ ይገንዩ ወይትማሐለሉ ዘምስለ ገዓር ወብካይ ውስተ መካነ ጎልጎታ ኀበ ተቀብረ ስምዐ ኮኑ እለ ሀየ ነበሩ፡፡ ወይቤሉ በማኅትወ ፋሲካ ዘቅድመ ትንሣኤ እንተ ይእቲ ሰንበተ ቀዳም ዘሰሙነ ሕማማቲሁ ይከውን ጉባኤ ክርስቲያን ውስተ መካነ ጎልጎታ ወይሰቅሉ ቀናዲለ በበጾታሆሙ፡፡ቅድመ የዐውዱ ሰብአ ሮም ወመለካውያን ወኢያስተርኢ ማኅቶተ ብርሃን በዑደቶሙ ወይወፅኡ ኀፋራኒሆሙ፡፡ ወእምዝ የዐውዱ ኢትዮጵያ ወግብጽ ወሶርያ ወአርማንያ ወማርናን፡፡ ወለእመ አልቦ ኢትዮጵያዊ ምስሌሆሙ ኢያስተርኢ ማኅቶተ ብርሃን ውስተ ቀናድሊሆሙ፡ወእመሂ ቦ ኢትዮጵያዊ ምስሌሆሙ ወኢይነብር ማኅቶተ ብርሃን ዘእንበለ ኀበ ቀንዲል ዘኢትዮጵያ፡፡ወእመሂ አፍለስዎ በዓመፀ መስተካህዳን ኀበ ካልዕ ገጽ መካን ይተልዎ ገጸ እግዚአብሔር ወያስተርኢ ዲቤሁ ማኅቶተ ብርሃን፡፡

፶፮ ናሁ አብጻሕነ ለክሙ ስምዐ በእንተ ዕበያ ወክብራ ለኢትዮጵያ፡፡እስመ ቦ እለ ዜነዉነ

የንጉሥ ሰዎች ማለት ነውና የኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች ማለትም አይደለም ቅጣትና- ስደትን ስለ መፍራት ንጉሥ መርቅያን ወደወደደው ተመልሰዋልና ስለዚህም ንጉሣውያን ተባሉ.ክርስቶሳውያን ግን አይደሉም መላኪ ማለት በዐረብ ቋንቋ ንጉሥ ማለት ነውና የሃይማኖታቸው ስያሜ ክህደታቸውን ያሳውቃልና ለእግዚአብሔርም ከሚያደሉ ይልቅ ለንጉሥ አድልተዋልና፡፡

፶፬ ወደ ሮም ንጉሥና ወደ ቍስጥንጥንያው ሊቀጳጳሳት ወደ ጉባኤያተኞቻቸውም ሁሉ ታሪካቸው ነገር እንመለስ፡፡ንስሓ ገብተው ከረከሰች ሃይማኖታቸው በሚመለሱ ገንዘብ በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት መሠዊያ ላይ የመንፈስ ቅዱሳን መውረድ ባዩ ጊዜ ሰይጣን በአፋቸው እፍ ያለባቸውን የሐሰት መጽሐፍ የሆኑ መጽሐፎቻቸውን ወደ ጥልቅ ባሕር ይወረውራሉ፡፡ዳግመኛም ክህደትን ያስተማራቸው አባታቸው ልዮንን ይረግሙታል፡፡ ከዚህም በኋላ ፍቅርና ስምምነት ሰላምም በኢትዮጵያ ንጉሥና በሮም ንጉሥ መካከል ይሆናል ይኸውም የአንበሳ ደቦል ነው፡፡ የኢየሩሳሌምም መንግሥት ወደ ሮም ንጉሥ ይመለሳል የምሥርና የግብጽ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ይመለሳሉ ከዚህ በኋላ የመነኮሳት አለቃ የባሕታውያንም አባት የሆነ አባ ሲኖዳ እንደተናገረ በሰላም ወደየሀገሮቻቸው ይመለሳሉ፡፡

፶፭ ኢትዮጵያውያን በፊቱ ይገዛሉ ጠላቶቹም አመድን ይቅማሉ ለማለት ሁለተኛም ዳግመኛ ትርጉም አለው ወደ ኢየሩሳሌም የሚሄዱ የኢትዮጵያ ስደተኞች ጌታ በተወለደበት ሥፍራ በቤተልሔም ይሰግዳሉ ይገዛሉ ይሰግዳሉም በተጠመቀበት በዮርዳኖስ ወንዝም ይታጠባሉ በተሰቀለበት ሥፍራ በቀራንዮ ይገዛሉ ይሰግዳሉም፡፡ሁለተኛም ከእንደገና ይገዛሉ ከፍጹም ልቅሶ ጋር በተቀበረበት ሥፍራ በጎልጎታ ይማልላሉ ከዚያም የነበሩት ምስክር ሆኑ አሉ፡፡ ከትንሣኤ በፊት በፋሲካ ዋዜማ ይህችውም የሕማማት ቀዳሚት ሰንበት ናት፣በጎልጎታ ሥፍራ የክርስቲያን ጉባኤ ይደርጋል በየወገናቸውም መብራት ይሰቅላሉ መጀመሪያም የሮም ሰዎችና መለካውያን ይዞራሉ ሲዞሩም ብርሃን አይገለጥም አፍረውም ይመለሳሉ ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያና የግብጽ ሶርያና አርማንያ ማርናም ይዞራሉ፡ ከእነርሱ ጋር ኢትዮጵያዊ ከሌለ በመብራቶቻቸው ውስጥ ብርሃን አይታይም ከእነርሱም ኢትዮጵያዊ ቢኖር በኢትዮጵያዊው መብራት ካልሆነ በቀር ብርሃን አይቀመጥም በዓመፁም ከሀዲዎች ወደ ሌላ ሥፍራ ቢያዘዋውሩት እንኳን የእግዚአብሔር ፊት ይከተለዋል በርሱም ላይ የሚያበራው መብራት ይታያል፡፡

፶፮ እነሆ ስለኢትዮጵያ ከፍ ከፍ ማለትና ስለ ክብሯ ምስክርነትን አደረስንላችሁ፡

ከመ ኀጥኡ ሰብአ ግብጽ እምፈላስያነ ኢትዮጵያ ወያዱ ባሕቲቶሙ ወኢያስተርአየ ሎሙ ማኅቶተ ብርሃኖሙ፡፡ወእምዝ ይቤልዎሙ ተንበላት እለ ይቀንይዎሙ ናሁኬ አሕሰምክሙ ሃይማኖተክሙ ወበእንተዝ ኢያስተርአየ ለክሙ ማኅቶተ አምላክክሙ እንከሰኬ ንመይጠክሙ ኀበ ሃይማኖትነ፡፡ወበከዩ ሰብአ ግብጽ እንዘ ይብሉ ኅድጉ ንስቲተ ከመ ንስአሎ ለአምላክነ፡፡ ወእምዝ ሶበ ኀደግዎሙ ሖሩ ኀበ መቃብሪሁ ለ፩ ፈላሲ እም ሰብአ ኢትዮጵያ ከረዩ ወአውፅኡ አዕጽምቲሁ ወቈጸርዎ በልብሶሙ ወያድዎ ለመቃብረ እግዚእነ በከመ ያለምዱ ለለዓመት፡፡ ወአስተርአየ ማኅቶተ ብርሃን ውስተ ቀንዲል፡፡ ወእምዝ ተፈሥሑ ሰብአ ግብጽ በእግዚአብሔር ዘረድኦሙ፡፡ ወተንባላትሂ ኀደግዎሙ ከመ ይንበሩ በሃይማኖቶሙ፡፡

፶፯ ንትመየጥኬ ኀበ ዘለፋሁ ለፎጢኖስ ዘእምረሳዕናሁ በበአተ ነገር ውስተ ካልዕ ፍና፡፡ ንበሎኬ ለፎጢኖስ ኦ ፎጢኖስ ከልብ ዘአብደ ያደውዮ ለዘነሰኮ ወበዕዐር ደዌ ይመውት ዘለከፎ በአስናኒሁ፡፡ ወከማሁ ዘሂ ይሰምዕ ትምህርተከ ይደዊ በሕማመ ስሕተትከ ይበውእ ሕምዘ ግዘት ውስተ ልቡ ዘይሰብር አዕጽምተ ወይመትር አማዑተ፡፡ ኦ ፎጢኖስ እፎኑ ትብሎ ለፈ እግርያም ህላዌሁ ለክርስቶስ ዘበእንቲአሁ ይቤ አብ በመጽሐፈ ሕግ አዳም ኮነ ከመ ፩ እምኔነ፡፡ ዘፍ፫፥፳፪

፶፰ ዳዊትኒ ይቤ ወእምቅድመ ፀሐይ ሀሎ ስሙ፡፡ዮሐንስኒ ወንጌላዊ ይቤ ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ወውእቱ ቃል ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል፡፡ ወከማሁ እምቀዲሙ ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ፡፡ ናሁኬ ይነግር ቅድመ ህላዌሁ ምስለ አብ፡፡ወእምዝ ያተሉ እንዘ ይብል ዘቦቱ ኵሉ ኮነ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ፡፡ ናሁኬ አግሀደ ከመ አልቦ ዘተገብረ በህላዌ ባሕቲቱ አብ ዘእንበለ ጽምረተ ወልድ፡፡ ወበእንተዝ ይቤ ዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ፡፡ ካዕበ ይቤ ዮሐንስ በውስተ መልእክቱ ዝ ውእቱ ቀደማዊ ዘሰማዕነ ወዘርኢነ ወዘጠየቅነ ወገሰሳ እደዊነ በእንተ ነገረ ሕይወት ወሕይወትኒ ተዐውቀት ለነ፡፡ መዝ፸፩፥፲፯ዮሐ፩፥፩ ፩ዮሐ፩፥፩

፶፱ ጳውሎስኒ ይቤ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘትማልም ወዮም ወክመ ውእቱ እስከ ለዓለም ፡፡ማርቆስኒ ይቤ ቀዳሚሁ ለወንጌል ኢየሱስ ክርስቶስ በከመ ጽሑፍ ውስተ መጽሐፈ ነቢያት፡፡ ካዕበ ይቤ በወንጌል ለእግዚአብሔርሰ አልቦ ዘርእዮ ግሙራ ወባሕቱ ወልድ ዘሀሎ ውስተ ሕጽኑ ውእቱ ነገረነ፡፡ ማር፩፥፩ ዮሐ፩፥፲፰ ዕብ፲፫፥፰

ግብጻውያን ከኢትዮጵያ መንገደኞች ሰው አጥተው ብቻቸውን እንደዞሩ የመብራታቸውም ብርሃን እንዳልታየላቸው የነገሩን ሰዎች አሉና፡፡ ከዚያም የሚገዙአቸው እስላሞች እነሆ ሃይማኖታችሁን አክፋፋችሁ ስለዚህም የአምላካችሁ ብርሃን አልተገለጠላችሁም ከእንግዲህስ ወደሃይማኖታችን እንመልሳችኋለን አሉአቸው፡ የግብጽ ሰዎችም አምላካችንን እንለምነው ዘንድ ጥቂት ጊዜ ተዉን ብለው አለቀሱ ከዚያም በተዉአቸው ጊዜ ከኢትዮጵያ ሰዎች ወገን ወደሆነ የአንድ መንገደኛ መቃብር ሄደው ቆፍረው አጥንቶቹን አወጡ በልብሳቸውም ቋጠሩት በየዓመቱም እንዳስለመዱት የጌታችንን መቃብር ዞሩት የመብራቱም ብርሃን በቀንዲሉ ውስጥ ታየ ከዚህም በኋላ የግብጽ ሰዎች በረዳቸው በእግዚአብሔር ደስ ተሰኙ እስላሞችም በሃይማኖታቸው እንዲኖሩ ተዉአቸው፡፡

፶፯ በነገር ወደሌላ ጉዳና መግባት ከረሳንበት ወደ ፎጢኖስ ተግሣጽ እንመለስ፡ ፎጢኖስን እንንዲህ እንበለው፣ፎጢኖስ ሆይ ያበደ ወሻ የነከሰውን ለሕመም ይዳርገዋል፡በጥርሶቹ የነካው እርሱ በአስጨናቂ ደዌ ተይዞ ይሞታል፡፡ እንደዚሁም ትምህርትህን የሚሰማ በስህተትህ ሕመም ይታመማል አጥንትን የሚሰብር አንጀትንም የሚቆርጥ የውግዘት መርዝ ወደ ልቡ ይገባል፣ ፎጢኖስ ሆይ በሕግ መጽሐፍ አብ ስለርሱ አዳም ከእኛ እንደአንዱ ሆነ ብሎ የተናገረለትን የክርስቶስን ህልውና እንደምን ከማርያም ከተወለደ ወዲህ ነው ትለዋለህ፡፡ ዘፍ፫፥፳፪

፶፰ ዳዊትም ከፀሐይ አስቀድሞ ስሙ አለ ወንጌላዊ ዮሐንስም በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ቃል እግዚአብሔር ነው እንደዚሁም ከመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ አለ፡፡እነሆ ከአብ ጋር የህልውናውን ቀዳሚነት ተናገረ ከዚያም ሁሉ በእርሱ የሆነ ያለርሱ የሆነ የለም ብሎ አስከተለ፡ እነሆ ያለ ወልድ አንድነት በአብ ብቻ ህልውና የተፈጠረ እንደሌለ ገለጠ፡፡ ዳግመኛም ዮሐንስ በመልእክቱ የሰማነውና ያየነው የተረዳነው እጆቻችንም የዳሰሱት ስለ ሕይወት ነገር ቀዳማዊ ይህ ነው ሕይወትም ተገለጠችልን አለ፡፡ መዝ፸፩፥፲፯ ዮሐ፩፥፩ ፩ዮሐ፩፥፩

፶፱ ጳውሎስም ኢየሱስ ክርስቶስ ትናትናና ዛሬ እስከ ዘላለም ድረስ ያው ነው አለ፡፡ ማርቆስም በነቢያት መጽሐፍ እንደተጻፈ ኢየሱስ ክርስቶስ የወንጌል መጀመሪያው ነው አለ፡፡ ሁለተኛም በወንጌል እግዚአብሔርን ያየው ፈጽሞ የለም ነገር ግን በእቅፉ ያለ እርሱ ነገረን አለ፡፡ ማር፩፥፩ ዮሐ፩፥፲፰ ዕብ፲፫፥፰

፷ ይሁዳኒ ይቤ ወአዘከረከሙ ፈቀድኩ
ወታእምሩ ምዕረሰ ከመ ኢየሱስ አድኀነ ሕዝቦ
እምድረ ግብጽ ወበዳግምሰ ለእለ ኢአምኑ አጥፍ
ኦሙ፡ ካዕበ ይቤ ዳዊት ምስሌከ ቀዳማዊ በዕለተ
ኃይል፡ በብርሃናሙ ለቅዱሳን። ለሊሁኒ ይቤ
ወልድ ሰብሐኒ አባ በስብሐትየ ዘሀሎ ምስሌከ
እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም። በዝኒ ኢትሌቡኑ
ኦ ፎጢኖስ ዕውረ ልብ ትትከሐድኑ በእንተ
ህላዌሁ ዘእምቅድመ ዓለም። መዝ፻፱፥፫ ዮሐ፲፯፥
፭ ይሁ ቁ..፭

፷፩ ኦ ፎጢኖስ ተክለ ሐሰት ተመላ
ሕከ እምሥርወ ሕያዋን ወተተከልከ ውስተ አዕ
ጻዳቲሆሙ ለዓጸውተ ሲኦል። ወንሕነሰ ነአምን
ከመ አብ ህልው ምስለ ወልዱ ወምስለ መንፈስ
ቅዱስ።አኮ ለመርድአ ግብር ዘወለዶ ለወልዱ
ወአኮ ለአስተዋፅኦ ኪን ወተግባር ዘተደመረ ህላ
ዌሁ ለመንፈስቅዱስ ውስተ ህላዌሁ አላ ፩
እሙንቱ ኅቡራነ ህላዌ ወኅቡራነ ግዕዝ ወሥር
ዓት።ኢርኩባን ለጠባይዐ ፍጥረት ኢልኩፋን
ለግሰተ አጻብዕ ኢያስተርእዩ ለንጻሬ ወኢይት
ሌበዉ ለእማሬ።ኢይትከወሱ በቱሳሔ ወኢይት
ፈለጡ በቡዓዴ ወኢይትሌዐሉ በፍድፋዴ። ወኢ
የሐጽጹ በኑታጌ።ኀሩም አብ ዮኢያስተርኢ በህላ
ዌሁ ዘእንበለ ዳእሙ በራእየ ትንቢት ለነቢ
ያቲሁ። ኅሩም ወልድ ዘኢያስተርኢ በመለኮቱ
ዘእንበለ በትስብእቱ።ኅሩም መንፈስቅዱስ ዘኢ
ያስተርኢ በካልዕ ግርማሁ ዘእንበለ ዳእሙ
በንጻሬ ዘይትፈቀድ በዘይረድኦሙ ለቅዱሳን።
ወሶበ ርእየ እግዚአብሔር ከመ ኢበቍዐ ደመ
አቤል ጻድቅ ለሥላጤ ዕዳሁ ለአዳም ኢሰኪቦቱ
ለይስሐቅ ዲበ ምሥዋዕ ዘነደቀ አቡሁ ወኢደመ
ናቡቴ እስራኤላዊ ዘተቀትለ በእንተ ዓጸደ ወይኑ
ኢደመ ኢሳይያስ ዘሰጠቅዎ ለለክፍል በሞሰርተ
ዕፅ፣ ወኢደመ ኤርምያስ ዘወደይዎ ውስተ ዓዘ
ቅተ ዓምዓም ሶበ ተነበየ በእንተ ጼዋዌ። ወእም
ድኅረ ሚጠተ ጼዋዌ ወገርዎ በአእባን ሶበ ይብል
አምላክ ወልደ አምላክ።ወይቤሉ ዝንቱ ውእቱ
ነገሩ ለኢሳይያስ አብዱ ላዕሌሁ ወቀተልዎ። ወዓ
ዲ ኢበቍዐ በአተ ፫ ደቂቅ ውስተ እቶነ እሳት
ዘባቢሎን ዘአፍልሕዎ በተይ ወፒሳ ወአስፈሊ
ጦን ወአቀላሚዶን እስከ ተለዐለ ነበለባሉ እም
አፈ እቶን ፵ወ፱ በእምት።ወኢበአተ ዳንኤል
ውስተ ግበ አናብስት ርኁባን። ሶበ ኀየለ መዳ
ልወ ኃጢአቶሙ ለአዳም ወለሔዋን እመዳልወ
ጽድቆሙ ለነቢያት ወእመዳልወ ደሞሙ ለቅ
ዱሳን ልዑል እስመ ምክንያተ ፀአቶሙ እምገነት
ለአዳም ወለሔዋን ኮነ በፈቲወ ከዊነ አምላክ።
ርእየ እግዚአብሔር ከመ ኢይሠልጥ ዕዳሁ ለፈ
ቲወ ከዊነ አምላክ ዘእንበለ ዳእሙ በደመ
አምላክ ከመ ኢይሠልጥ ዕዳሁ ለፈቲወ ከዊነ
አምላክ ዘእንበለ ዳእሙ በደመ አምላክ። ኀደረ
አቡሃ ለሔዋን ኀበ ወለተ ሔዋን ጽሕቀ አቡሁ
ለአዳም ለከዊነ ዳግም አዳም። ናሁኬ ያርኢ

፷ ይሁዳም ኢየሱስ ሕዝቡን ከግብጽ
ምድር እንዳዳነ ላሳስባችሁ ፈጽማችሁም እን
ድታውቁም ወደድሁ፡በሁለተኛውም ያላመኑትን
አጠፋቸው አለ።ሁለተኛም ዳዊት በኃይል ቀን
ከአንተ ጋር ቀዳማዊ ነው፡የቅዱሳንም ብርሃናቸ
ው አለ።እርሱም ራሱ ወልድ አባት ሆይ ዓለም
ሳይፈጠር አስቀድሞ ከአንተ ጋር በነበረ ክብሬ
አክብረኝ አለ።ልብህ የታወረ ፎጢኖስ ሆይ በዚህ
አታስተውልምን ከዓለም አስቀድሞ ስላለ ህልው
ናው ትክዳለህን።መዝ፻፱፥፫ ዮሐ፲፯፥፭ ይሁ ቁ..፭

፷፩ የሐሰት ተክል ፎጢኖስ ሆይ
ከሕያዋን ሥር ተነቅለህ በሲኦል በረኞች አፀዶች
ውስጥ ተተከልህ፡እኛ ግን አብ ከልጁና ከመንፈስ
ቅዱስ ጋር እንዳለ እናምናለን። ልጁን የወለደው
ለሥራ ረዳትነት አይደለም የመንፈስቅዱስም ህ
ልውና አንድ የሆነው ጥበብና ሥራ ለማዋጣት
አይደለም፡በህልውና የሚተባበሩ በባሕርይና በሥ
ርዓት የተባበሩ አንድ ናቸው እንጂ።ለፍጥረታት
ጠባይ አይገኙም፡በጣት ለመዳሰስ የማይነኩ ለእ
ይታ የማይታዩ ለማመልከትም በማስተዋል የማ
ይወሰኑ ናቸው፣ በጭማሪ አይናወጹም በመነጠ
ልም አይለዩም በመብዛትም ከፍ አይሉም በመ
ጉደሉም አይጉድሉም ለነቢያቱ በትንቢት ራእይ
እንጂ በባሕርዩ የማይታይ አብ ልዩ ነው በሰ
ውነቱ ካልሆነ በቀር በመለኮቱ የማይታይ ወልድ
ልዩ ነው።ቅዱሳንን በሚረዳቸው ገንዘብ በሚፈ
ለግ እይታ እንጂ በልዩ ግርማው የማይታይ
መንፈስቅዱስ የተለየ ነው።እግዚአብሔር የጻድቁ
የአቤል ደም የአዳምን ዕዳ ለመክፈል እንዳል
ጠቀመ ባወቀ ጊዜ የይስሐቅም አባቱ በሠራው
መሠዊያ ላይ መተኛት፡ ስለወይን ቦታው የተገ
ደለ የእስራኤላዊው የናቡቴም ደም፡ በእንጨት
መጋዝ በየጥቂቱ የሰነጠቁት የኢሳይያስ ደም፡ስለ
ምርኮ ትንቢት በተናገረ ጊዜ ረግረግ ወዳለበት
ጉድጓድ የከተቱት የኤርምያስ ደም፡ ከምርኮ
ከተመለሰም በኋላ የአምላክ ልጅ አምላክ ባለ
ጊዜ በደንጊያ ወገሩት ይህ የኢሳይያስ ነገር ነው
አሉ በርሱም ላይ ተቆጡ ገደሉትም። ደግመኛም
የሦስቱ ልጆች አርባ ዘጠኝ ክንድ ወደላይ ነበልባ
ሉ ከእቶኑ አፍ ከፍ እስኪል ድረስ በተይና በፒሳ
በአስፈሊጦንና በአቅላሚዶን ወዳፈሉት የባቢሎን
የእሳት እቶን መግባት የዳንኤልም ወደተራቡ
የአንበሶች ጉድጓድ መጣል አልጠቀመም። የአዳ
ምና የሔዋን የኃጢአታቸው ሚዛን ከነቢያት
የጽድቃቸው ሚዛን ከልዑል ቅዱሳንም የደማ
ቸው ሚዛን በበለጠ ጊዜ የአዳምና የሔዋን
ከገነት የመውጣት ምክንያት አምላክ ለመሆን
በመሻት ነውና እግዘብሔር በአምላክ ደም
ካልሆነ በቀር አምላክ ለመሆን የመሻትን ዕዳ
እንደማይከፍል ዐወቀ፣ የሔዋን አባት በሔዋን
ሴት ልጅ ዘንድ አደረ የአዳም አባቱ ዳግማይ
አዳም ለመሆን ተጋ፣ እነሆ የእግዚአብሔር በረከ
ት ከሕዝብ ወደ ሕዝብ ሲፋለስ ያሳያል የአቤልን

እንዘ ይትፋለስ በረከተ እግዚአብሔር እምሕዝብ ውስተ ሕዝብ::መሥዋዕተ አቤል ተወክፈ ወዘቃየልሰ ኢተወክፈ ወበእንተዝ በቅንዓት ቀተሎ ቃየል ለአቤል:በቀለ ደሙ ጸርሐ ወሰከየ እንዋሁ ኀበ እግዚአብሔር እስከ ረገማ እግዚአብሔር ለምድር ዘይገብር ቃየል::ዘፍ፫÷፩፣፬÷፰ ፩ነገ ፰÷፲፩ ኤርሚ፫÷፩ ዳንኗ÷፳፪ ዕብ፲፩÷፴፮

መሥዋዕት ተቀበለ የቃየልን ግን አልተቀበለም ስለዚህም ቃየል በቅናት አቤልን ገደለው ቃየል የሚያርሳትን ምድር እግዚአብሔር እስከረገማት ድረስ ደሙ ለበቀል በእግዚአብሔር ዘንድ ጮኸ ወንድሙንም ከሰሰ:: ዘፍ፫÷፩፣፬÷፰ ፩ነገ ፰÷፲፩ ኤርሚ፫÷፩ ዳንኗ÷፳፪ ዕብ፲፩÷፴፮

፳፫ ወበእንተዝ አስተማሰለ ጳውሎስ ደመ ኢየሱስ ክርስቶስ በደመ አቤል ጻድቅ ወይቤ በንዝኀተ ደም ነባቢ ዘይኄይስ እምተናግሮ እምዘአቤል::ወእምድኅረ ሞቱ ለአቤል ተወልደ ሴት ዘበትርጓሜሁ ተክለ ህየንተ አቤል ዘቀተሎ ቃየል ወበእንተዝ አዕረፈ በረከተ አቤል ላዕለ ደቂቀ ሴት:: ወዘርአ ቃየልሰ ኮነ ለመርገም ወለድምሳሴ እምገጸ ምድር:: ወለደ ኖኅ ፫ ደቂቀ ሴምሃ ወካምሃ ወያፌትሃ:: ወለካምሰ ውኅደት በረከቱ ወለያፌትሂ ይቤሎ ለያርኅብ እግዚአብሔር ምድረ ለያፌት::ወለሴምሰ ይቤሎ አቅዲሙ እምበረከተ ያፌት ይትባረክ እግዚአብሔር አምላኩ ለሴም:: ወእምድኅረ በረከተ ያፌትኒ አትለወ ወይቤ ለይኅድር እግዚአብሔር ውስተ ቤቱ ለሴም::ናሁ ተመክዐበ በረከት ወተዐውቀ ከመ የኀድር እግዚአብሔር ውስተ ቤቱ:ናሁኬ ፈለሰት በረከት ኀበ ቤተ ሴም:: ዘፍ፱÷፳፮ ዕብ፲፪÷፳፬

፳፫ ስለዚህም ነገር ጳውሎስ ከአቤል መናገር የሚሻል የሚናገረውን ደም በመርጨት ብሎ የኢየሱስ ክርስቶስን ደም በጻድቁ በአቤል ደም መስሎ ተናገረ::ከአቤል ሞት በኋላ ሴት ተወለደ: ትርጉሙም ፈንታ ምትክ ማለት ነው ስለዚህም የአቤል በረከት በሴት ልጆች ላይ አረፈ የቃየል ዘር ግን ለርግማንና ከምድር ለመ ጥፋት ሆነ:: ኖኅ ሦስት ልጆችን ሴምና ካምን ያፌትንም ወለደ:የካም በረከቱ ጠፋች ያፌትንም እግዚአብሔር የያፌትን ምድር ያስፋ አለው፣ ሴምን ግን ከያፌት በረከት አስበልጦ የሴም አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን አለ:: ከያፌት ምርቃትም አስከትሎ እግዚአብሔር በሴም ቤት ይደር አለ::እነሆ በረከት እጥፍ ድርብ ሆነ እግዚአብሔር በቤቱ እንደሚያድር ታወቀ እነሆ በረከት ወደ ሴም ቤት ገባች:: ዘፍ፱÷፳፮ ዕብ፲፪÷፳፬

፳፬ ወለደ አብርሃም እስማዔልሃ እም አጋር ግብጻዊት ወይስሐቅሃ ዘበርስዓን እምሳራ ወለተ አቡሁ:: ዮቃጢንሃ ወዝንባሪሃ ወያክሶንሃ ወማይዳንሃ ወኢዮዝባቅሃ ወሴሐሃ እምኬጡራ:: ወፈለሰት በረከት ኀበ ይስሐቅ ወልደ ሳራ እስመ ይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም እምይስሐቅ ይሰመይ ለከ ዘርአ:: ዘፍ፲፯÷፲፭ ፣፳፭÷፲፪

፳፬ አብርሃም ከግብጻዊቷ አጋር እስማኤልን ከአባቱ ሴት ልጅ ከሳራም በርጅናው ወራት ይስሐቅን ወለደ:: ዮቃጤንና ዝንባሪን ያክሶንና ማይዳንን ኢዮዝባቅና ሴሔን ከኬጡራ ወለደ:: በረከት ወደ ሳራ ልጅ ወደ ይስሐቅ አለፈች እግዚአብሔር አብርሃምን ከይስሐቅ ዘር ይጠራልሀል ብሎታልና:: ዘፍ፲፯÷፲፭ ፣፳፭÷፲፪

፳፭ ወለደ ይስሐቅ ዔሳውሃ ወያዕቆብሃ:: ወይቤ እግዚአብሔር በአፈ ነቢይ ያዕቆብሃ አፍቀርኩ ወዔሳውሃ ጸላዕኩ:: ናሁኬ ተግሕሰ በረከተ እግዚአብሔር እምዔሳው ኀበ ያዕቆብ::ወለደ ያዕቆብ ፲ወ፪ ደቂቀ ወለለ ፩ ፩ አርአየ ያዕቆብ በረከቶሙ ከመ ሀብተ ጸጋ ዘይደልዎሙ:: ለይሁዳሰ ይቤሎ ይሁዳ ሰብሑከ አኀዊከ እደዊከ ዲበ ዘባኖሙ ለጸላዕትከ::ይሰግዱ ለከ ደቂቀ አቡከ ይሁዳ እጓለ አንበሳ ለከብከ ወኖምከ ከመ አንበሳ ወከመ እጓለ አንበሳ አልቦ ዘያነቅሀከ::ኢይጠፍእ ምልክና እምይሁዳ ወም ስፍና እምአባሉ እስከ አመ ይረክብ ዘጽኑሕ ሎቱ::ውእቱ ተስፋሆሙ ለአሕዛብ የሐጽብ በወ ይን ልብሶ በደመ አስካል ሰንዱኖ::የአሥር በሐ ረገ ወይን አድኀ ወበዕፀ ኤሎቅ ዕዋሎ::ፍሡ ሐት እምወይን አዕይንቲሁ ወጸዓዳ ከመ ሐሊብ ስነኒሁ:: ዘፍ ፵፱÷፩-፳፰ ዕብ፩÷፪

፳፭ ይስሐቅም ዔሳውና ያዕቆብን ወለደ እግዚአብሔርም በነቢይ አፍ ያዕቆብን ወደድሁ ዔሳውን ግን ጠላሁ ብሎ ተናገረ እነሆ የእግዚአብሔር በረከት ከዔሳው ወደ ያዕቆብ ዘወር አለ:: ያዕቆብ አስራሁለት ልጆችን ወለደ:ለእያንዳንዳቸውም እንደሚገባቸው የጸጋ ሀብት በረከታቸውን አሳየ::ይሁዳን ይሁዳ ወንድሞችህ ያመስግኑህ እጆችህ በጠላቶችህ ጀርባ ላይ ናቸው:: የአባትህ ልጆች ይሰግዱልሀል:ይሁዳ የአንበሳ ደቦል እንደ አንበሳ ተኛህ አንቀላፋህም እንደ አንበሳም ደቦል የሚቀሰቅስህ የለም:መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም ግዛትም ከወገኑ:ገዥ የሆነው እስኪመጣ ድረስ:እርሱ የአሕዛብ ተስፋቸው ነው ልብሱን በወይን ያጥባል መደረቢያውንም በፍሬ ደም:: አህያውን በወይን ሐረግ ውርንጭላውንም በወይን ሐረግ ያሥራል:ዓይኖቹ ከወይን ይልቅ ደስ ያሰኛሉ ጥርሶቹም እንደወተት ነጭ ናቸው አለው:: ዘፍ፵፱÷፩-፳፰ ዕብ፩÷፪

፳፮ ናሁኬ አስተርአየ ትእምርተ መን
ግሥቱ ለክርስቶስ ውስተ ቤተ ይሁዳ።ወይሁዳኒ
ወለደ ዛራሃ ወፋሬስሃ እምትዕማር ብእሲተ ኤር
ወአውናን።ወፋሬስኒ ወለዶ ለኤስሮም ወኤስሮ
ምኒ ወለዶ ለአራም ወአራምኒ ወለዶ ለአሚናዳበ
ወአሚናዳብኒ ወለዶሙ ለነአሶን ወለኤልሳቤጥ
ብእሲተ አሮን ካህን።ወነአሶንሰ መልአከ ኃይሎ
ሙ ውእቱ ለቤተ ይሁዳ ወውእቱ ወለዶ ለሰሎ
ሞን።ወሰሎሞንኒ ወለዶ ለባዖስ እምረአብ ዘማ
ዘኢያሪኮ እንተ ይእቲ ደወለ ጋይ። ወባዖስኒ
ወለደ ኢዮቤድሃ እምነ ሩት ሞአባዊት፡ወኢዮቤ
ድኒ ወለደ ዕሤይሃ። ወዕሤይኒ ወለደ ኤልያብሃ
በኵሪ ወአሚናዳብሃ ካልዐ ስማዕሃ ሣልሰ ናት
ናኤልሃ ራብዖ ራዳይሃ ኀምሰ ነአሶንሃ ሳድሰ ዳዊ
ትሃ ሳብዖ። ማቴ፩፥፫-፮

፳፯ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሳሙኤል
ምላእ ቀርነ ቅብዕ ወሑር ኀበ ቤተልሔም ወባእ
ቤተ ዕሤይ ወአነ አርእየከ ዘኀረይኩ እምደቂቁ።
ወበጽሐ ሳሙኤል ውስተ ቤተልሔም ወቦአ
ውስተ አፀዱ ለዕሤይ ወይቤሎ አምጽዖሙ ለደቂ
ቅከ ወአምጽአ ለኤልያብ ወይቤ ሳሙኤል ዝኑ
መሲሑ ለእግዚአብሔር። ወይቤ እግዚአብሔር
አኮ ዘንተ ዘኀረይኩ።ወካዕበ አምጽአ ሳሙኤል
ለአሚናዳብ ወአርአዮ ቅድመ እግዚአብሔር ወይ
ቤ እግዚአብሔር ለዝኒ ኢኀረይክዎ።ወአምጽኦ
ሙ ዕሤይ ለስድስቲሆሙ ደቂቁ ወኢያስተርአየ
ገጸ እግዚአብሔር ምስሌሆሙ በቅድመ ሳሙኤ
ል።

፳፰ ወይቤሎ ሳሙኤል ለዕሤይ
ኢሀሎኑ ለከ ካልዕ ዘእንበለ እሉ።ወይቤሎ ዕሤይ
ለሳሙኤል ሀሎ ወልድ ንኡስ ዘይሬዒ መራዕየ
አባግዕየ።ወይቤሎ ሳሙኤል ለአክአብ ያምጽእዎ
ፍጡነ።ወአምጽእዎ ለዳዊት ወአቀምዎ ቅድመ
ሳሙኤል።ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሳሙኤል ዝ
ውእቱ ዘእቤለከ።ተንሥእ ቅብዖ።ወበካልዕኒ ይብ
ል ወረከብክዎ ለዳዊት ገብርየ ወቀባዕክዎ ቅብዐ
ቅዱሰ።እስመ እዴየ ትረድኦ ወመዝራዕትየ ታጸ
ንዖ፡ወኢይበቍዕ ጸላዒ በላዕሌሁ ወውሉደ ዐመፃ
ኢይደግም አሕምሞቶ።ወእመትሮሙ ለፀሩ በቅ
ድመ ገጹ።ወአኀሥሮሙ ለጸላዕቱ። ወሣህልየሰ
ወጽድቅየ ምስሌሁ፡ ወበስምየ ይትሌዓል ቀርኑ።
ወእሠይም ውስተ ባሕር እዴሁ ወውስተ አፍላ
ግ የማኖ፡ውእቱ ይብለኒ አቡየ አንተ ወአነሂ
በኵርየ እሬስዮ፡ወልዑል እምነ ነገሥተ ምድር።
፩ሳሙ፲፮፥፩-፲፫ መዝ፹፰፥፳

፳፱ ወበካልዕኒ ይብል ወአነ
አበቍል ቀርነ ለዳዊት፡ወአስተዴሉ ማኅቶተ ለመ
ሲሕየ፡ ወአለብሶሙ ኀፍረተ ለጸላዕቱ፡ወቦቱ ይፈ
ሪ ቅድሳትየ፡ወበካልዕኒ ይብል ወይገብር ምሕረቶ
ለመሲሑ፡ ለዳዊት ወለዘርኡ እስከ ለዓለም።
መዝ፲፯፥፶፤፻፴፩፥፲፯

፳፮ እነሆ የክርስቶስ የመንግሥቱ
ምልክት በይሁዳ ቤት ታየ ይሁዳም ዛራንና ፋሬ
ስን ከኤርና ከአውናን ሚስት ከትዕማር ወለደ፣
ፋሬስም ኤስሮምን ወለደ ኤስሮምም አራምን
ወለደ አራምም አሚናዳብን ወለደ አሚናዳብም
ነአሶንንና የካህኑ የአሮንን ሚስት ኤልሳቤጥን
ወለዳቸው ነአሶን የይሁዳ ቤት አለቃቸው ነው።
እርሱም ሰሎሞንን ወለደ ሰሎሞንም የጋይ አው
ራጃ ከሆነች ከኢያሪኮ አመንዝራ ከረአብ ባዖስን
ወለደ ባዖስም ከሞአባዊቷ ከሩት ኢዮቤድን ወለ
ደ ኢዮቤድም ዕሤይን ወለደ ዕሤይም የበኵር
ልጁ ኤልያብን ሁለተኛውንም አሚናዳብን ሦስተ
ኛውንም ስማዕን አራተኛውን ናትናኤልን አም
ስተኛውን ራዳይን ስድስተኛውን ነአሶንን ሰባተኛ
ውንም ዳዊትን ወለደ። ማቴ፩፥፫-፮

፳፯ እግዚአብሔር ሳሙኤልን
የዘይቱን ቀንድ ይዘህ ወደ ቤተልሔም ሂድ ወደ
ዕሤይም ቤት ግባ እኔም ከልጆቹ የመረጥሁትን
አሳይሀለሁ አለው።ሳሙኤል ቤተልሔም ደረሰ
ወደ ዕሤይ አፀድ ገብቶ ልጆችህን አምጣቸው
አለው፣ኤልያብን አመጣው ሳሙኤልም የእግዚአ
ብሔር መሲሕ ይህ ነውን አለ እግዚአብሔር ግ
ን የመረጥሁት ይህንን አይደለም አለ።ሁለተኛም
ሳሙኤል አሚናዳብን አምጥቶ በእግዚአብሔር
ፊት አቆመው እግዚአብሔርም ይህንንም አልመ
ረጥሁትም አለ።ዕሤይ ስድስቱንም ልጆቹን አመ
ጣቸው በሳሙኤል ፊት የእግዚአብሔር ገጽ
ከእነርሱ አልታየም።

፳፰ ሳሙኤል ዕሤይን ከእነዚህ ሌላ የለ
ህምን አለው፣ዕሤይም የበጎች መንጋ የሚጠብቅ
ታናሽ ብላቴና አለ አለው።ሳሙኤልም ፈጥነው
እንዲያመጡት ላከ አለው፡ዳዊትንም አመጡት
በሳሙኤልም ፊት አቆሙት።እግዚአብሔርም ሳሙ
ኤልን የነገርሁህ ይህ ነው ተነሥና ቅባው አለው
በሌላም መጽሐፍ አገልጋዬ ዳዊትን አገኘሁት
የተቀደሰውንም ቅባት ቀባሁት እጄ ትረዳዋለች
ና ክንዴም ታበረታዋለች፡ጠላት በርሱ ላይ አይ
ሠለጥንም የዓመፃም ልጆች ዳግመኛ አይሠቀዩ
ትም ጠላቶቹን በፊቱ አዋርዳቸዋለሁ የሚጠሉ
ትንም አጕሳቍላቸዋለሁ ይቅርታዬና ጽድቄ
ከእርሱ ጋር ይሆናል በስሜም ቀንዱ ከፍ ከፍ
ይላል እጁን በባሕር ላይ እሾማለሁ ቀኙንም በወ
ንዞች ላይ፡እርሱ አንተ አባቴ ነህ ይለኛል እኔም
በኵር አደርገዋለሁ ከምድር ነገሥታት ይልቅ
ከፍ ከፍ ያለ ነው ይላል። ፩ሳሙ፲፮፥፩-፲፫
መዝ፹፰፥፳

፳፱ በሌላም እኔም ለዳዊት ቀንድን
አበቅላለሁ ለቀባሁትም መብራትን አዘጋጅለታ
ለሁ ጠላቶቹን እፍረትን አለብሳቸዋለሁ በርሱም
ቅድስናዬ ያፈራል ይላል።በሌላም ሥፍራ ምሕ
ረቱን ለተቀባው ያደርጋል ለዳዊትና ለዘሩ እስ
ከ ዘላለም ድረስ ይላል። መዝ፲፯፥፶፤፻፴፩ ፥፲፯

፸ ኢሳይያስኒ ይቤ ትወጽእ በትር እምሥርወ ዕሤይ፡ ወየዓርግ ጽጌ እምጕንዱ ፡ ወየዐርፍ ዲቤሁ መንፈሰ እግዚአብሔር፡፡ ናሁኬ ፈለሰት በረከተ እግዚአብሔር ኀበ ቤተ ዳዊት፡፡ ቀርነ ቅብዕ ፈልሐ ዲበ ርእሱ ወበትረ መንግሥት ሠረፀት እምቤቱ፡፡ወእም ዘርአ ዚአሁ አንሥአ ለነ እግዚአብሔር ቀርነ መድኃኒትነ፡፡ ወዓዲ ኢቦአ ውስተ አዕጻዳቲሆሙ ለነገሥተ ገሊላ ኢኀረያ ለወለተ ሄሮድስ፡፡ወለተ ነዳያን ኀረየ እም ወለተ ዐበይቶሙ ለነገሥተ ይሁዳ፣እንዘ እግዚአብሔር ውእቱ ውስተ ማኅፀነ ብእሲት ኅደረ፡፡

፸፩ ወሶበሂ አፍቀረ ወፈተወ ሥና ኢያዕረጋ ሰማያተ ከመ ትኩኖ እመ በጽርሐ አርያም፡ አላ ለሊሁ ወረደ ወኅደረ ውስተ ቤተ ዮሴፍ ፀራቢ፡፡ ኢያንበራ ዲበ ሰረገላ ዘኪሩቤል ከመ ትፅንሶ በህየ፡ አላ ለሊሁ ኅደረ ውስተ ማኅፀና እንዘ ሀለወት በሀገረ ገሊላ እንተ ስማ ናዝሬት፡፡ ኢያስተሳተፋ በዕበዩ እመ ሥጋዌሁ ወኢይቤሎ ለገብርኤል አምጽኣ ዝየ ለድንግል ከመ ትፁረኒ በከርሣ ፱ አውራኃ፡ አላ ለሊሁ ተሳተፈ ትሕትናሃ ወረደ ምስለ ገብርኤል ወቦአ ውስተ ቤተ ንዴታ፡፡ ወሶበ ይቤላ መልአክ መንፈስቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ ተቀደሰት በርደተ መንፈስቅዱስ ለከዊነ እመ አምላክ፡፡ ወሶበ ደገመ ብሂሎታ ኃይለ ልዑል ይጼልለኪ ጸንዓት ለጸዊረ ወልድ ዋሕድ በኃይለ አቡሁ ሰማያዊ፡፡ ወሶበ ይቤላ ወዘኒ ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ ወይሰመይ ወልደ ልዑል፡፡ ውእቱ ዘይትወለድ እምኔሃ፡፡አዕረገት ሕሊናሃ ውስተ ጽርሐ አርያም ኀበ ሀሎ ወልድ ምስለ አቡሁ፡፡ ውእቱኒ አጽነነ ሰማያተ ወወረደ ወሦጠ ርእሶ ውስተ ማኅፀና፡፡

፸፪ ወካዕበ ትቤሎ ድንግል ለመልአክ ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ፡፡ ውእተ ጊዜ ተሠገወ ቃል እምኔሃ፡፡ ኢያምጽአ ምስሌሁ አመ ሥጋዌሁ ፬ እንስሳሁ ርእያ ከመ ኢትደንግፅ ወነጺራ ከመ ኢትፍራህ፡፡ ኀደገ ህየ ሰማያውያነ እለ በሥርዓተ ሰማይ ዕቁባነ፡፡ ወገብረ በዝየ ሥርዓተ ምድራዊተ ዘይበቍዕ ለመልእክተ ቅዱሳን፡፡ ህየ ህልው በየማነ አቡሁ ወበዝየ ህልው በውስተ ማኅፀነ እሙ፡፡ ህየ ባሕቲቱ ኃይል ዘኢያስተርኢ ወበዝየ ኃይል ዘኢይትገሰስ ምስለ ሥጋሁ ዘይትገሰስ፡፡ህየ መጸር ፬ እንስሳ ዘሥዕለ እሳት ወበዝየ ፬ መጸር ጠባይዕ ዘፍና ትስብእት፡፡ ህየ አብ ዘእንበለ እም ወበዝየ እም ዘእንበለ አብ ምድራዊ፡፡ ህየ ገብርኤል ይቀውም በፍርሀት ወበዝየ ገብርኤል ያበስር በትፍሥሕት፡፡ህየ ስብሐተ ልደት እምአብ ወኢያስተርኢ ዘይትነከር በጽርሐ አርያም ወዝየ ስብሐተ ልደት እምድንግል ዘይትነከር በቤተልሔም፡፡ ሉቃ፩፥፲፱፣፳፯

፸ ኢሳይያስም ከዕሤይ ሥር በትር ትወጣለች ከግንዱም አበባ ይወጣል በርሱም ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ ያርፋል አለ፡፡ እነሆ የእግዚአብሔር በረከት ወደዳዊት ቤት አለፈች የዘይቱ ቀንድ በራሱ ላይ ፈላ የመንግሥትም በትር ከቤቱ በቀለች ከዘሩም እግዚአብሔር የመድኃኒታችንን ቀንድ አነሣልን ዳግምኛም ወደ ገሊላ ነገሥታት አፀዶች አልገባም የሄሮድስን ሴት ልጅ አልመረጣትም ከይሁዳ ነገሥታት ከታላላቆች ሴት ልጅ ይልቅ በሴት ማኅፀን ውስጥ አደረ፡፡

፸፩ በወደዳትና ደምግባቷን በወደደ ጊዜም በጽርሐ አርያም እናት ትሆነው ዘንድ ወደ ሰማይ አላሳረጋትም እርሱ ራሱ ወረደ በጠራቢው በዮሴፍም ቤት አደረ እንጂ፡፡ በዚያ ትፀንሰው ዘንድ በኪሩቤል ሠረገላ ላይ አላስቀመጣትም ናዝሬት በተባለች በገሊላ ሀገር ሳለች እርሱ ራሱ በማኅፀኗ አደረ እንጂ፡፡ሰው ሲሆን ጌትነቱን አላሳተፋትም ገብርኤልንም ዘጠኝ ወር በማኅፀን እንድትሸከመው ድንግልን ወደዚህ አምጣት አላለውም እርሱ ራሱ ትሕትናዋን ተሳተፈ እንጂ፡ ከገብርኤል ጋር ወረደ ወደ ችግርም ቤት ገባ መልአኩም መንፈስቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል ባላት ጊዜ የአምላክ እናት ለመሆን በመንፈስ ቅዱስ ተቀደሰች ደግሞም የልዑል ኃይል ይጋርድሻል ባላት ጊዜ አንድ ወልድን በሰማያዊ አባቱ ኃይል ለመሸከም ጸናች፡፡ይህም ካንቺ የሚወለደው ቅዱስ ነው የልዑል ልጅ ይባላል ሲላት ያን ጊዜ ከእርሷ የሚወለደው የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አስተዋለች ኅሊናዋን ወልድ ከአባቱ ጋር ወዳለበት ወደ ጽርሐ አርያም አሳረገች እርሱም ዝቅ ብሎ ከሰማያት ወረደ ራሱንም በማኅፀኗ ውስጥ አሳደረ፡፡

፸፪ ዳግመኛም ድንግል መልአኩን እንዳልሽኝ ይሁንልኝ አለችው ያን ጊዜ ቃል ከእርሷ ሥጋን ተዋሐደ አይታ እንዳትደነግጥ ተመልክታም እንዳትፈራ ሰው በሆነ ጊዜ ከእርሱ ጋር አራቱን እንስሳውን አላመጣም በሰማይ ሥርዓት የተጠበቁ ሰማያውያኑን በዚያ ተው፡፡በዚህም ለቅዱሳን መልእክት የሚረባ ምድራዊት ሥርዓትን ሠራ በዚያ በአባቱ ቀኝ አለ በዚህም በእናቱ ማኅፀን ውስጥ አለ፡፡በዚያ ብቻውን የማይታይ ኃይል ነው በዚህም የማይዳሰስ ኃይል ከሥጋው ጋር የሚዳሰስ ሆነ በዚያ ተሸካሚዎቹ እሳት የተሣለባቸው አራቱ እንሰሳ ናቸው፡፡በዚህም ተሸካሚዎቹ ሰው በመሆን መንገድ የተገቡ አራት ጠባያት ናቸው፡፡በዚያ ያለ እናት አባት አለው በዚህም ያለምድራዊ አባት እናት አላችው፡በዚያ ገብርኤል በፍርሀት ይቆማል በዚህም ገብርኤል በሐሤት የምሥራች ይናገራል በዚያ በጽርሐ አርያም የሚደነቅ ከማይታይ አብ የመወለድ ምስጋና በዚህም በቤተልሔም የሚደነቅ ከድንግል የመወለድ ምስ ጋና አለው፡፡ ሉቃ፩፥፲፱፣፳፯

፸፫ ሀየ መዓዛ ዕጣን ይትቄረብ በስያሐ ወርቅ እምካህናት ሰማያውያን ወበዝየ ይትቄረብ ወርቅ ወከርቤ ወስኂን እምሰብአ ሰገል::ሀየ ኪሩቤል ወሱራፌል ይርዕዱ እምግርማሁ ወበዝየ ማርያም ተሐቅፎ ወሰሎሜ ትትለአኮ::ሀየ ንጥረ መባርቅት ያንበሰብሱ ቅድሜሁ ወላህበ እሳት ይወጽእ እምጽርሑ ወበዝየ አድግ ወላህም ያስተማውቅዎ በእስትንፋሶሙ::ሀየ መንበረ እሳት ወበዝየ ጎለ እብን::ሀየ ጽፍጸፈ ሰማይ ዘእብነ በረድ ወበዝየ ምጽንጋዕ ዘአልህምት::ሀየ ኢየሩሳሌም እንተ በሰማያት መካነ ትጉሃን ወበዝየ በዓት ማኅደሮሙ ለኖሎተ እንስሳ::ሀየ ብሉየ መዋዕል ዘዳንኤል ዘኢይትዓወቅ ኑኃ መዋዕሊሁ ወዝየ ዮሴፍ አረጋይ ይጸውሮ ዘበዓቅመ እጓለ እመሕያው ትልቄ ዓመታቲሁ::

፸፬ ሶበሰ በጽርሐ አርያም ፀንሰቶ እምኮና ክብረ ወልዕልና ለባሕቲታ:: ንሕነሰ እም ኢረከብነ በቍዔተ በልዕልናሃ::ምንተ ነአምር ምሥጢረ ዘበሰማያት ይትገበር ወምንተ ንሬኢ ኅቡአተ ዘበአርያም ሀሉ::ሶበሂ ዲበ ሠረገላ ኪሩቤል ወለደቶ መኑ እምርእየ ሑቃፌሁ ወመኑ እምገሰሶ ሥጋዌሁ::ሶበሂ ኢያንሶሰወ ዲበ ምድር መኑ እምአርአየ አሠረ ተጠምቆ ወላዕለ መኑ እምኮነ ስምዐ አብ እንዘ ይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ወሎቱ ስምዕዎ፡ ወዲበ ርእሰ መኑ እምወረደ መንፈስቅዱስ በርእየተ ርግብ ጸዓዳ:: ወእመሰ ኢያስተርአየ ጾታ ሥላሴ በስመ መኑ እምተጠመቅነ:: ወበእንበይነዝ ይቤሎሙ ለአርዳኢሁ ሑሩ ወስብኩ ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ:: ወከመ ኢይበሉ መኑ አብ ወመኑ ወልድ ወመኑ መንፈስቅዱስ አርአየ ጾታ ሥላሴ በፈለገ ዮርዳኖስ::ወእመሂኬ ኢወርዘወ በአምጣነ ብእሲ ወኢያስተርአየ በአካለ እጓለ እመ ሕያው መኑ እም ሐመ በእንተ መድኃኒትነ:: ናሁኬ ክብረ እጓለ እመሕያው እምትጉሃነ ሰማይ እስመ እግዚአብሔር ተወልደ እምብእሲት:: ወበእንተዝ ይቤ ጳውሎስ ዘአኮ መላእክተ ተወክፈ አላ ዘርአ አብርሃም አልዐለ:: ኢሳ፮፥፩ ዳን፯፥፱ማቴ፫፥፲፫ ሉቃ፱፥፲፭ ዕብ፩፥፲፮

፸፭ ወይእዜኒ ፈጺመነ ዘለፋሁ ለፎጢኖስ ንግበር በዓለ ሥጋዌሁ ለወልደ አምላክ፡ ንትጋነይ ለማኅፀን እንተ ጾረቶ፡ ወንሰግድ ለአብራክ እለ ሐቀፋሁ፡ ንዘምር ለአጥባት እለ ሐፀናሁ፡ ወናእኵት ለአእዳው እለ ለከፋሁ፡ ወንየብብ ለከናፍር እለ ሰዓማሁ፡ ንሰብሕ ምስለ ኖሎት ወነአምኅ ምስለ ሰብአ ሰገል:: ናንክርኬ ከመ ዮሴፍ ንትለአክ ከመ ሰሎሜ፡ ናስተብርክ ውስተ ጎል ኀበ ሰከበ፡ ናንገርግር ውስተ ምጽን

፸፫ በዚያ ከሰማያውያን ካህናት በወርቅ ማዕጠንት የዕጣኑን መዓዛ ይቀበላል::በዚህም ወርቅና ከርቤን ሽቱንም ከሰብአ ሰገል ተቀበለ::በዚያ ኪሩቤልና ሱራፌል ከግርማው የተነሣ ይንቀጠቀጣሉ በዚህም ማርያም አቀፈችው ሰሎሜም አገለገለችው፡በዚያ የመብረቆች ብልጭልጭታ በፊቱ ይገላለጣሉ የእሳትም ወላፈን ከአዳራሹ ይወጣል በዚህም አህያና ላም በትንፋሻቸው አሟሟቁት በዚያ የእሳት ዙፋን አለ በዚህም የደንጊያ በረት፡በዚያ የዕብነ በረድ የሰማይ ንጣፍ በዚህም የላሞች መጠጊያ በረት በዚያ የትጉሃን ሥፍራ በሰማያት ያለች ኢየሩሳሌም አለችው በዚህም የእንስሳት ጠባቂዎች ማደሪያ በዓት አለው በዚያ የዘመኑ ርዝማኔ የማይታወቅ የዳንኤል ሽማግሌ አባት አለው በዚህም የዓመቶቹ ቁጥር በሰው ልጅ አቅም መጠን የሆነ ሽማግሌ ዮሴፍ ተሸከመው::

፸፬ በጽርሐ አርያም ፀንሳው ቢሆን ክብርና ከፍ ከፍ ማለት ለብቻዋ በሆነ እኛም በርሷ ከፍ ማለት ጥቅም ባላገኘን ነበር በሰማያት የሚደረገውን ምሥጢር በምን እናውቃለን::በአርያም ያለውንስ የተሸሸገውን ምን እናያለን:: በኪሩቤል ሰረገላ ላይ ወልዳው ቢሆን መታቀፉን ማን ያይ ነበር ማንስ አካሉን ይዳስሰው ነበር::በምድር ላይ ባይመላለስ የመጠመቅን ፍለጋ ማን ያሳይ ነበር:: አብስ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት ብሎ በማን ላይ ምስክር ይሆን ነበር መንፈስቅዱስም በነጭ ርግብ አምሳል በማን ላይ ይወርድ ነበር:: የሥላሴ አካል ባይገለጥ በማን ስም እንጠመቅ ነበር:: ስለዚህም ደቀመዛሙርቱን ወደ ዓለም ዳርቻዎች ሄዳችሁ አስተምሩ ስታጠምቁአቸውም በአብና በወልድ በመንፈስቅዱስም ስም በሉ አላቸው::አብ ማን ነው ወልድስ ማን ነው መንፈስቅዱስስ ማን ነው እንዳይሉ በዮርዳኖስ ወንዝ የሥላሴን አካል ገለጠ:: በሰው መጠን ጉልማሳ ባይሆን በሰው ልጆችም አካል ባይገለጥ እኛን ስለማዳን ማን መከራ በተቀበለ ነበር:: እነሆ ከሰማይ ትጉሃን ይልቅ የሰው ልጅ ከበረ እግዚአብሔር ከሴት ተወልዷልና::ስለዚህም ነገር ጳውሎስ መላእክትን የተቀበለ አይደለም የአብርሃምን ዘር ከፍ ከፍ አደረገ እንጂ አለ:: ኢሳ፮፥፩ዳን፯፥፱ማቴ፫፥፲፫ ሉቃ፱፥፲፭ ዕብ፩፥፲፮

፸፭ አሁንም የፎጢኖስን ተግሣጽ ፈጽመን የአምላክን ልጅ ሰው መሆኑን በዓል እናድርግ የተሸከመችውን ማኅፀን እናመስግን ላቀፋት ጉልበቶች እንስገድ ላሳደጉት ጡቶች እንዘምር የዳሰሱትን እጆች እናመስግን ለሳሙት ከንፈሮች እናሸብሽብ ከእረኞች ጋር ምስጋናን እናቅርብ ከሰብአ ሰገልም ጋር እጅ እንንሣ እንደ ዮሴፍ እናድንቅ እንደ ሰሎሜም እናገልግል በተኛበት በረት እንስገድ በተጠቀለለበት በረት እን

ጋዕ ኀበ ተጠብለለ፡ወንበል ስብሐት ለእግዚአ ብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ለዘሠመሮ ለሰብእ፡ እግዚአብሔር ኮነ ሰብአ ወወለተ እጓለ እመሕያው ኮነት እመ እግዚአብሔር፡ሎቱ ስብ ሐት ወላቲ ስግደት ለዓለመ ዓለም አሜን፡ ወአሜን፡፡

፳፯ ተፈጸመ ዘለፋሁ ለፎጢኖስ ሐረገ ገሞራ፡ ለኀብለ ሃይማኖት ዘመተራ፡ ለመለ ኮተ ወልድ ዘአስተናከራ ለቤተ ክርስቲያን ዘአስ ተሐቀራ፡ይቤ ጊዮርጊስ ዘሀገረ አምሐራ፡ ወልደ ትምህርቶሙ ለካህናተ ደብተራ ለፍኖተ ሃይማ ኖት ዘአፍቀራ፡ ሰአሉ ሎቱ አባግዐ ምሥጢር ውሉደ ቅድስት ቀልብንጥራ፡፡ ከመ ታስተሥሪ ኃጣውኢሁ ድንግል ኀበ በኵራ፡በዝኒ ዓለም ከመ ትባልሖ እመከራ፡ ወበዘይመጽእ ዓለም ከመ ታብእ ውስተ ማኅደራ፡ ወታብልዖ እማዕደ ሕይ ወት ዘነከራ፡ታስትዮ እምወይነ ምሥጢራ፡ ወታግሕሦ እምአንቀጸ ደይን ከመ አይርአይ ግሙራ፡ ዘንተ መጽሐፈ አዘዘ ከመ ይትነበብ በዕ ለተ ተዝካራ፡ አመ ፳ወ፱ ለታኅሣሥ እንተ ባቲ አስተርአየ ዕበየ ክብራ፡ ወተሰብሐ ስነ ምግባራ፡ ለዓለመ ዓለም አሜን፡ ወአሜን፡፡ ኢሳ፯÷፬ ዳን፯÷፱ ማቴ፫÷፲፫ ሉቃ፪÷፲፩ ዕብ፩÷፲፮

........ /// ..........

ንበርከክ ለእግዚአብሔር በሰማያት ምስጋና ይሁን በምድርም ሰውን ለወደደው እንበል፡፡ እግዚአብሔር ሰው ሆነ የሴት ልጅም የእግዚአብ ሔር እናት ሆነች ለርሱ ምስጋና ይሁን ለእር ሱም ስግደት ይገባል ለዘላለሙ አሜን፡ ይሁን፡፡

፳፯ የሃይማኖትን ገመድ የቆረጣት የወልድንም መለኮት የለያት ቤተ ክርስቲያንንም ያቃለላት የገሞራ ሐረግ የፎጢኖስ ተግሣጽ ተፈጸመ፡፡ የቤተ መቅደስ ካህናት የትምህርት ልጃቸው የሃይማኖትን መንገድ የወደዳት በአማራ ሀገር የሚኖር ጊዮርጊስ ተናገረው፡፡ የቅድስት ቤተክርስቲያን ልጆች የምሥጢር መንጋ ድንግል ከልጇ ዘንድ ኃጢአቶቹን ታስተሠርይለት ዘንድ ለምኑለት በዚህ ዓለም ከመከራ ታድነው ዘንድ በሚመጣውም ዓለም ወደ ማደሪያዋ ታስገባው ዘንድ ከመንፈስ ቅዱስም የሕይወት ማዕድ ታበላው ዘንድ ከምሥጢር ወይኗም ታጠጣው ዘንድ ከፍ ርድ ቦታ ደጃፍም ፈጽሞ እንዳያይ ታርቀው ዘንድ ይህን መጽሐፍ በመታሰቢያዋ ቀን የክብሯ ታላቅነት በታየበት የሥራዋም በጎነት በተመ ሰገነበት በታኅሣስ ሃያ ዘጠኝ ቀን እንዲነበብ አዘ ዘ ለዘላለሙ አሜን፡፡ ኢሳ፯÷፬ ዳን፯÷፱ ማቴ፫÷፲፫ ሉቃ፪÷፲፩ ዕብ፩÷፲፮

........ /// ..........